## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን

# የ1999 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ

# የትምህርትና ቅስቀሳ መሪ ሰነድ




1999 ዓ.ም.
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዓላማ፡-

"ለአስተዳደራዊ ጉዳዮችና ለምርጫዎች፣ ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለዕቅድ አፈፃፀም፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ለምርምር የሚጠቅሙ ሕዝብን የሚመለከቱ መረጃዎችን በቆጠራ መሰብሰብ፣ ማጠናቀር መገምገምና ማሰራጨት ነው።" የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማቋቋያ አዋጅ ቁጥር 449/97

# ማውጫ

ገጽ

I. መግቢያ ........ 1
II. የሕዝብ ቆጠራ አጭር ታሪካዊ ምልክት ........ 1
III. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተሞክሮ በኢትዮጵያ ........ 3
IV. የዘመናዊ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም ........ 4
V. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሲካሄድ ማሟላት ያለበት ዋና ዋና ጉዳዮች ........ 4
VI. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ባህሪያት ........ 5
VII. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አዋጅ ........ 5
VIII. የ1998 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ........ 5
i. የቆጠራው አስፈላጊነት ........ 5
ii. የሕዝብና ቤት ቆጠራው የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ........ 6
iii. በቆጠራው የሚሠማራው የሰው ኃይል ብዛት ........ 9
iv. ቆጠራው የሚሸፍነው አካባቢ ........ 9
v. ቆጠራውን የሚያካሂደው ማን ነው ........ 10
IX. የሕዝብና ቤት ቆጠራው ሥራ መዋቅር እና የተለያዩ ኮሚቴዎች አደረጃጀት ........ 10
X. የሕዝብና ቤት ቆጠራው ሥራ ለማካሄድ የሚከናወኑና የተከናወኑ አበይት ቅድመ ዝግጅቶች ........ 11
ሀ. የቆጠራው ዕቅድ ዝግጅት ........ 11
ለ. የቆጠራው የጊዜ ሰሌዳ ........ 12
ሐ. የውጭ ዕርዳታ ስለማግኘት ........ 12
መ. የቆጠራ ካርታ ሥራ ........ 12
ሠ. የመጠይቆች ዝግጅት ........ 14
ረ. ልዩ ዝግጅት የሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ቆጠራ ........ 14
መጠለያ የሌላቸው ነዋሪዎች
የጋርዮሽ መኖሪያ ነዋሪዎች
የውጭ አገር ዜጎች
የአርብቶ አደር አካባቢ ለመቁጠር የተካሄደ ጥናት ........
ሰ. የሙከራ ቆጠራ ማካሄድ ........ 15
ሸ. የሠራተኞች ምልመላ ሥልጠናና ሥምሪት ........ 16
መጠይቆችንና ማቴሪያሎችን ወደ መስክ ማድረስ

ቀ. የመረጃ ቅንብር ዝግጅት ............ 17
በ. በቆጠራው የሚሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነት ............ 18
XI. በቆጠራው ቀናት የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታና የሚጠበቅ ትብብር ............ 21
ሀ. መረጃውን የሚሰበስቡት እነማን ናቸው? ............ 21
ለ. መረጃዎቹ የሚሰበሰቡት እንዴት ነው? ............ 21
ሐ. ቆጠራው የሚካሄደው መቼ ነው? ............ 22
መ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ መርሆዎች ............ 22
ሠ. ከሕዝብና ቤት ቆራ የሚገኙት መረጃዎች በሚስጥር
የሚጠበቁ ስለመሆናቸው ............ 24
ረ. ቆጠራው እንዲሳካ ከህብረተሰቡ የሚጠበቅ ትብብር ............ 25
ሰ. በየደረጃው ከሚገኙ የመስተዳደር አካላት የሚጠበቅ ትብብር
ሸ. ግዴታና ቅጣት ............ 26
XII. የህዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርት ቅስቀሳ ዓላማ
ሀ. የትምህርትና ቅስቀሳ ዓላማ ............ 27
ለ. የትምህርትና ቅስቀሳ ዘዴዎች ............ 28
ሐ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ አፈፃፀም ሁኔታ ............ 29
መ. በቅስቀሳ ተግባር ላይ የሚሳተፉ አካላት ............ 29
ሠ. በትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ላይ የልዩ ልዩ አካላት ሚና ............ 30
XIII. የድህረ ቆጠራ ተግባራትን ስለማካሄድ ............ 33
ሀ. መረጃውን በኮምፒውተር ማቀነባበር ............ 33
ለ. ድህረ ቆጠራ ጥናት ማከናወን ............ 34
ሐ. የቆጠራውን ወጤት መገምገም፣ መተንተን ሪፖርት ማዘጋጀት ............ 34
መ. የቆጠራውን ውጤት ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ............ 34

## I. መግቢያ

1. የአንድን ሀገር የልማት ዕድገት አቅጣጫ የሚመራ የመነሻ ዕቅድ፣ ፖሊሲና እስትራቴጂ አስፈላጊነቱ እሙን ነው። ይህ መነሻ ዕቅድ፣ ፖሊሲና እስትራቴጂ የሚዘጋጀውም የየወቅቱን ተጨባጭ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ከሚያንፀባርቀው ስታቲስቲካዊ መረጃ በመነሳት ነው። በሌላ አነጋገር በዕቅድ የሚመራ የትኛውም የልማት ዘርፍ የሚራመድበትን ረጅም የእድገት ጉዞ በመተለም በየዕርከኖቹ የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች እያስወገደ ወደታሰበው የእድገት ግብ ለመሸጋገር ይበቃ ዘንድ ከሁሉ በፊት ትክክለኛ መረጃ ሊኖረው ይገባል። ባለንበት ፈጣን ዘመን ልማትና ብልጽግና ሊረጋገጥ የሚችልበትን ፕሮግራምና ፖሊሲ ለመንደፍ የእድገት እቅድን ለማዘጋጀትና በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ተከታትሎ ውጤቱን ለመገምገም የስታቲስቲክስ መረጃዎች አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይደለም።

2. በየዓመቱና ከዚያም በታች እንደአስፈላጊነቱ በየሦስት፣ አምስት ወይም አሥር ዓመት የሚሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የአንድን ሀገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የሥነ-ሕዝብ ተጨባጭ እውነቶች ስለሚያንፀባርቁ የአጠቃላዩን የመንግሥት የልማት መርሐ-ግብር ለመገምገምና ለመከታተል ለግባትነት የሚያገለግሉ ከመሆናቸውም በላይ ለተለያዩ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና ተመራማሪዎች ለጥናቶቻቸው መሠረት በመሆን ያገለግላሉ።

3. በጠቅላላ ቆጠራ፣ በናሙና ጥናት፣ አስተዳደራዊ መዛግብትና የማያቋርጥ የልደት፣ የሞት ... ወዘተ ምዝገባ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን በመጠቀም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ዲሞግራፊያዊ መረጃዎች የሚሰበሰቡ ሲሆን ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች መካከል ሕዝብና ቤትን በተመለከተ እንደ አብይ ምንጭና መሠረት ሆኖ የሚያገለግለው አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ነው።

4 እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል በቆጠራው ላይ የሚጠበቅበትን ትብብር እንዲያደርግ ስለቆጠራው ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ ስለቆጠራው ሂደት፣ ... ወዘተ በመሳሰሉት ላይ ትምህርት መስጠትና መቀስቀስ አስፈላጊ ነው።

## II. የሕዝብ ቆጠራ አጭር ታሪካዊ ምልከታ

5. የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በልዩ ልዩ ምክንያትና ለተለያዩ ፍላጐቶች ራሱንና በዙሪያው የሚገኙ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን መጠን ለማወቅ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ቆጠራዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል። ይህም የሚያመለክተው የሰው ልጅና የመረጃ

ፍላጐት ጥምረታቸው ከጥንት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ነው። የተለያዩ የጽሁፍ ማስረጃዎች እንደሚያመላክቱት ከጥንት ጀምሮ በልዩ ልዩ ሃገሮች የሕዝብ ቆጠራዎች ይካሔዱ ነበር። በዋነኛነት የነዚህ ጥንታዊ የሕዝብ ቆጠራ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ነበሩ:-

- ግብር ለመሰብሰብ፣
- ለውትድርና ምልመላ እንዲሁም
- የሥራ ግዳጆችን ለመወጣት፣ ...ወዘተ ናቸው።

6. በእነዚህ ጥንታዊ ቆጠራዎች የሚሰበሰቡት መረጃዎች በአብዛኛው ትኩረት ያደርጉ የነበረው በቤተሰብ ኃላፊ፣ በግብር ከፋይ ወይም ለውትድርና ምልመላ እንዲያመች በጐልማሳ ነዋሪዎች ላይ ብቻ ነበር። ስለዚህም እነዚህ ጥንታዊዎቹ የሕዝብ ቆጠራ ሙከራዎች ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማካተት የተከናወኑ አልነበሩም።

7. ከአንዳንድ ጥናቶች ለመረዳት እንደተቻለው የሕዝብ ቆጠራ በዓለም ውስጥ መቼ እንደተጀመረ ጊዜው በትክክል ባይታወቅም ከክርስቶስ ልደት በፊት ቆጠራ ያካሔዱ አገሮች እንደነበሩ ለማወቅ ይቻላል።

<u>ለምሳሌ:-</u>

- በባቢሎን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3,800 ዓመተ ዓለም፣
- በቻይና " " " በ3,600 ዓመተ ዓለም፣
- በግብፅ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2500 ዓመተ ዓለም እንዲሁም ጥንታዊያኑ ግሪክና ሮም በተደጋጋሚ ብዙ የህዝብ ቆጠራዎች እንዳካሔዱ ይነገራል። በነዚህ የሕዝብ ቆጠራዎች አማካኝነት የሚሰበሰቡት መረጃዎች ስለሕዝቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና ስለ ሌሎች መሰል ጉዳዮች የሚጠቁሙ ነበሩ።

8. በአንዳንድ የአውሮጳ አገሮች በተለይ በ14ኛውና በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ስለመሳፍንቱና ስለቀሳውስቱ ብዛት በመዝገብ ላይ ይሠፍር ነበር። ይሁን እንጂ እነዚህ ሙከራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ጠቅላላ የሕዝብን ብዛት ያካተተ ቆጠራ የተካሔደበት ጊዜ በጣም የተወሰነ እንደነበር ግልጽ ነው።

9. ዘመናዊ የሕዝብ ቆጠራ አመጣጥና እድገት ከላይ ከተጠቀሱት ሙከራዎች የሚነሳ ሆኖ ነገር ግን አሁን ለሚገኝበት ደረጃ ለመድረስ የወሰደው ጊዜ ረጅምና አዝጋሚ ነበር። የሕዝብ ቆጠራ ዓላማ ከመነሻውና ከአጀማመሩ ወታደሮችን ለመመልመልና ህዝቡን ግብር ለማስከፈል ሲባል ሲካሄድ የኖረ ቢሆንም በተለይ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ይዘቱን፣ የመረጃ አሰባሰብ ስልቱንና ሽፋኑን በማሻሻል እየተለወጠ በመምጣቱ ሌሎች የሕዝቡን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ መረጃዎችን በመጨመር ተጠናክሮ መከናወን ችሏል። ለምሳሌ

የሕዝብ ቆጠራው ስለአስተዳደር፣ ስለንግድ ሥራ፣ ስለትምህርት እንዲሁም፣ ለምርምርና ጥናት ወ.ዘ.ተ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ያካተቱ ጥያቄዎችን በመጨመር መካሔድ ጀመረ።

ይህን የተጠናከረ አሠራር በመከተል በሚከተሉት ሀገሮች በተለያየ ጊዜ የሕዝብ ቆጠራዎች ተካሒደዋል። እነዚህም፣

- በ1660 እ.ኤ.አ በኩቤክ
- በ1749 " በስዊድን
- በ1790 " በዩናይትድ ስቴትስ
- በ1801 " በእንግሊዝና በፈረንሳይ
- በ1863 " በናይጀሪያ
- በ1871 " በካናዳ
- በ1891 " በጋና
- በ1897 " በሩሲያ የተደረጉ ቆጠራዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

11. በ18ኛውና በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመንና ከዚያም በፊት ዘመናዊ የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድ የጀመሩ ሀገሮች በአሁኑ ጊዜ በየአምስት ወይም በየአሥር ዓመቱ ቆጠራ ያካሄዳሉ።

## III. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተሞክሮ በኢትዮጵያ

12. በሀገራችን በጥቂት አካባቢዎች ማለትም በአዲስ አበባና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች የሕዝብ ቆጠራዎች የተካሔዱ ሲሆን በተለይ በአዲስ አበባ በ1953 እና በ1961 ዓ.ም ቆጠራዎች እንደተካሔዱ ካለፈው የሀገሪቱ የቆጠራ ታሪክ መረዳት ተችሏል። በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሕዝብ ቆጠራ መስፈርትን ያሟላ ቆጠራ እንዲካሔድ ቀደም ካሉት ዓመታት ጀምሮ ሙከራዎች የተደረጉ ሲሆን በተለይ ቀደም ብሎ ጠቅላይ ስታቲስቲክስ ጽ/ቤት ተብሎ ይጠራ በነበረውና በአሁኑ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ አማካኝነት በአዋጅ ቁጥር 303/1964 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በ1968 ዓ.ም ቆጠራ ለማካሄድ ታስቦ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም በወቅቱ ያገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ማለትም የነበረው የመንግሥት ለውጥና ሌሎችም ሁኔታዎች ባለመፍቀዳቸው ቆጠራው በወቅቱ ሊካሔድ አልቻለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ የመጀመሪያውና ሳይንሳዊ የቆጠራ መስፈርቶችን ያሟላው የመጀመሪያው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በግንቦት ወር 1976 ዓ.ም ተካሔደ።

13. ቀደም ብሎ በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በየተወሰነ ወቅት ማካሔድ የሚያስፈልግ በመሆኑ ሁለተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ አሥረኛ ዓመቱን ጠብቆ በተጠናከረ ሁኔታ በጥቅምት ወር 1987 ዓ.ም ተካሒዷል። በአሁኑ ወቅትም የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት (የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ) ሦስተኛውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ በግንቦት ወር 1999 ዓ.ም ለማካሔድ በርካታ የዝግጅት ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።

## IV. *ዘመናዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም*

14. የሕዝብና ቤት ቆጠራ አጠር ባለ ሁኔታ ሲገለጽ "በተወሰነ ወቅትና በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በአገር ውስጥ በተወሰነ የአስተዳደር ክልል ስለአለው ሕዝብ ብዛት፣ ስለ ሕዝቡ የሥነ-ሕዝብ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት እንዲሁም በአገር አቀፍ ወይም በተወሰነ የአስተዳደር ክልል ስለሚገኙ ቤቶች ብዛት፣ ስለቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀርና ከዚያም አስተማማኝነቱንና ትክክለኛነቱን በመገምገም የተገኘውን ውጤት ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባራትን ያጠቃልላል።"

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት ከአነስተኛ የአስተዳደር ክልል ማለትም ከገጠር እና ከከተማ ቀበሌ አስተዳደር ጀምሮ እስከ ብሄራዊ ክልል ከዚያም በሀገር አቀፍ ደረጃ በገጠርና በከተማ መረጃዎችን ያስገኛል።

## V. *የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሲካሄድ መሟላት ያለባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች*

15. የህዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በጣም አስፈላጊ፣ ግዙፍ ሥራና ከፍተኛ ወጪ እንደዚሁም የድርጅቶችንና የግለሰቦችን ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ የሚከናወነው በመንግሥት ነው። ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የቆጠራው ሥራ በአዋጅ መደገፍ ስላለበት የሕዝብና ቤት ቆጠራ አዋጅ ማውጣት ያስፈልጋል።

16. የህዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ጥንቃቄን የሚጠይቅ፣ ረዥም ጊዜ የሚወስድ አድካሚና ውስብስብ በመሆኑ ሥራውን በአግባቡ አቅዶ የሚሠራ የተማረ የሰው ኃይል እና ቆጠራውን የሚያከናውን የሰው ኃይል በብዛትና በሙያ ዓይነት እንዲኖር ያስፈልጋል።

17. የህዝብና ቤት ቆጠራ ተግባር በጣም ሰፊ የዝግጅት ጊዜ ስለሚፈልግና ሰፊ ሽፋን ስላለው ብዙ ወጪ ይጠይቃል። ስለሆነም የህዝብና ቤት ቆጠራ ተግባራዊ ለማድረግ ከመንግስት በቂ በጀት ሊመደብለት ይገባል።

## VI. የህዝብና ቤት ቆጠራ ባህሪያት

18. ቆጠራው አንድ ወሰኑ በታወቀ የአስተዳደር ክልል ውስጥ ያለውን አካባቢ ሳይደጋገም ወይም ሳይዘለል ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት፡፡ ወሰኑ የታወቀ የአስተዳደር ክልል ማለትም ወረዳ፣ ከተማ፣ ዞን፣ ብሄራዊ ክልል ወይም ሀገርን ሙሉ በሙሉ የሚያጠቃልል መሆን አለበት፡፡

19. በቆጠራው የሚሰበሰበው መረጃ እያንዳንዱን ነዋሪ በነፍስ ወከፍ በየቤቱ ሄዶ በመጠየቅ የሚገኝ መሆን አለበት፡፡ ይህም ማለት የቀበሌውን ባለሥልጣን ወይም የመንደር ኃላፊውን ብቻ በመጠየቅ ስለቀበሌው ወይም ስለመንደሩ ነዋሪዎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎች መሰብሰብ አይኖርበትም ማለት ነው፡፡

20. ቆጠራው አንድ የተወሰነ ቀንና ሰዓትን በማስመልከት መረጃ የሚሰበሰብበትና በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ መሆን አለበት፡፡ ይኸውም ቆጠራው እንዲካሄድ በተወሰነው የቆጠራ ቀን (reference date) በአንድ በተወሰነ ቀን እኩለ ሌሊት በቤተሰቡ የተገኙትን አባላት ወይም በዚያ ሰዓት የቤተሰቡ መደበኛ አባላት የነበሩትን ብቻ ያጠቃልላል፡፡

በመሆኑም፣

- ከቆጠራው ቀን እኩለ ሌሊት በኋላ የሚወለደው ሕፃን በቆጠራው አይጠቃለልም፣
- ከቆጠራው ቀን እኩለ ሌሊት በፊት የሞተ ሰው በቆጠራው አይጠቃለልም

21. የሕዝብና ቤት ቆጠራ በአብዛኛው አገሮች በየአሥር ዓመት ይካሄዳል፡፡ በጥቂት አገሮች ደግሞ በየአምስት ዓመቱ ይካሄዳል፡፡ ቆጠራው በተወሰነ ወቅት እንዲደገም ከሚያስገድዱ ምክንያቶች አንዱ በተከታታይ በተካሄዱ ቆጠራዎች የተገኙትን መረጃዎች በማነፃፀር በሕዝቡ ብዛት ወይም በሕዝቡ ባሕርያት / የትምህርት ደረጃ፣ ልደት፣ በሞት ...... ወዘተ/ ላይ የሚከሰተውን ለውጥ ለመገምገም እንዲያስችል ነው፡፡

## VII. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈፀሚያ አዋጅ

22. የ1999 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማስፈፀም ይቻል ዘንድ በአዋጅ ቁጥር 449/1997 የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የተቋቋመ ሲሆን ተጠሪነቱም ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡

## VIII. *የ1999 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ*

### *ሀ. የቆጠራው አስፈላጊነት*

23. እስከ አሁን ድረስ በሃገራችን ሁለት ጊዜ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች ብቻ የተካሄዱ ሲሆን የመጀመሪያው በ1976 የሁለተኛዉ ደግሞ በ1987 ተካሂደዋል:: በመሆኑም ሁለተኛዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከተካሄደ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከአሥር ዓመት በላይ የሆነ ጊዜ ተቆጥሯል ማለት ነዉ:: በእነዚህ አመታት ውስጥ በአገሪቱ የሕዝብ ብዛት፣ ሥርጭት፣ ...... ወዘተ ላይ በርካታ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ለውጦች ተከስተዋል:: ስለዚህ ከ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተገኙትን መረጃዎች ወቅታዊ ለማድረግ፣ የተከሰቱትን ለውጦች ለመገምገም፣ አዳዲስ መረጃዎችንም በብቃትና በጥራት ለማሰባሰብ፣ የነዋሪውን የወደፊት የሥነ ሕዝብ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ባህርያትን አስተማማኝና ወቅታዊ ከሆኑ መረጃዎች በመነሣት ለመተንበይ፣ ...... ወዘተ. በ1999 ግንቦት ወር የሚካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ አስፈላጊ ነው::

## ለ. *የሕዝብና ቤት ቆጠራው የሚያስገኛቸው ጥቅሞች*

24. በሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ለሃገር ዕድገት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ማንኛዉም ሰዉ ፀቅድሚያ ሊገነዘበዉ ይገባል:: ከዚህ አንፃር ለሀገር ተቆርቋሪ ከሆነ ማንኛውም ዜጋ የሚጠበቀው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በሚካሄድበት ወቅት ትክክለኛና እውነተኛ የሆኑ መረጃዎችን በፈቃደኝነት ለቆጣሪው መስጠት ነው::

25. መንግሥት ምንግዜም ቢሆን ሕዝቡ የተሻለ ኑሮ እንዲኖረው ለማስቻል ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል:: በመሆኑም መንግሥት ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ መንገዶችን .... ወዘተ በበቂ መጠን እንዲሠራ ለማድረግ፣ እንዲሁም የሥራ መስኮችን በሚገባ ለመዘርጋትና ያሉትንም ለማስፋፋት እንዲችል ጠቅላላ የሕዝቡ ብዛት በሃገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተሞችና በሌሎችም አነስተኛ የአስተዳደር እርከኖች ደረጃ በቅድሚያ መታወቅ አለበት:: በመሆኑም የሕዝብና ቤት ቆጠራን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በሚገባ በመገንዘብ ፍሬአማና ትክክለኛ የሆነ ውጤት ለማግኘት ቆጠራውን ከፍ ባለ ጥንቃቄ ማካሄድ ያስፈልጋል:: ይህም ሊሆን የሚችለው እያንዳንዱ መልስ ሰጭ በሕዝብና ቤት ቆጠራ ለሚጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ለቆጣሪው ከሰጠ ብቻ ነው:: የሕዝብና ቤት ቆጠራው ተግባር በትክክልና በጥንቃቄ ተከናወነ ሊባል የሚችለው በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በሙሉ ሳይዘለሉና ሳይደገሙ ሲቆጠሩ ከመሆኑም በላይ መረጃዉን ለመሰብሰብ በተዘጋጀዉ መጠይቅ ዉስጥ ለተካተቱ ጥያቄዎችም ማንኛውም ነዋሪ ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃ ሲሰጥ ነው::

26. የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ጥቅም ከግል የዕለት ተዕለት ኑሮአችን ጋር እንዴት እንደሚያያዝ መገንዘብ ተገቢ ነው:: ለምሳሌ አንድ ቤተሰብ ሰባት አባሎች አሉት እንበል:: ይኸውም ባልና ሚስቱ እንደዚሁም አምስት ልጆቻቸው፣ እነኚህ ሰዎች በቀን በቀኑ ምግብ

መመገብ እንደሚያስፈልጋቸው የታወቀ ነው። ለምሳሌ አንድ ቀን ትልቁ ልጅ ለጨዋታ ወይም ትምህርት ቤት ሄዶ ሲመለስ ወላጆቹ ወንድሞቹና እህቶቹ ምግባቸውን ተመግበው የርሱን ድርሻ ረስተው ሳያስቀምጡ ቆዩት እንበል። ይህ ልጅ ወደ ቤት ተመልሶ ሲመጣ የሚበላ ምግብ እንዳልተቀመጠለት ሲያወቅ ምን ስሜት ይሰማዋል? ተገቢው ድርሻው አለመቀመጡ ሊያናድደው ይችላል። በተጨማሪም እናትየው ምግቡን በሥርዓት አቅዳ አለማዳረሷን ይገነዘባል። ምግቡ እንኳን በቂ ባይሆንም ከያንዳንዱ ድርሻ በመቀነስ ሁሉም ድርሻውን እንዲያገኝ ማድረግ ነበረባት እንጂ አንዱ ብቻ ምግብ ከነጭራሹ ሳያገኝ የቀሩት ሁሉ በቂ ምግብ እንዲያገኙ ማድረግ አይገባትም ነበር። እንግዲህ የአንድ ቤተሰብ እናት እንኳን የሠራችውን ምግብ በሥርዓት ለማዳረስ መመገብ ያለባቸውን የልጆቿን ብዛት ማወቅ ካስፈለጋት መንግሥት ደግሞ ለሕዝቡ አስፈላጊውን አገልግሎቶች ማለትም እንደ ትምህርት፣ ሕክምና፣ የሥራ ዕድል፣ የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎት፣ በቂ ምግብ፣ ለግብርና የሚያስፈልጉ አቅርቦቶች፣ የፖሊስ ጥበቃ፣ .... ወዘተ ለመስጠትና ለማዳረስ በጠቅላላ በአገሪቱ በየክልሉ፣ በየዞኑ፣ በየወረዳው እንደዚሁም በአነስተኛ አስተዳደር ክፍሎች የሚገኘውን ሕዝብ ብዛት ማወቅና እነዲሁም የሕዝቡን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ባሕርያት የሚገልጹ መረጃዎችን በተመለከተ ከፍተኛ ግንዛቤ እንዲኖረው ያስፈልጋል ማለት ነው።

27. በአንድ አስተዳደር ክልል ሆስፒታል ለመሥራትና የቀሩትንም የጤና አገልግሎቶች ለነዋሪው ለመስጠት በክልሉ የሚኖረውን ሕዝብ ብዛት ማወቅ አስፈላጊ ነው። እንደዚሁም ትምህርት ቤቶችን ለመሥራትና በቂ መምህራን ለማሰልጠን በትምህርት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ሕጻናት ብዛት ማወቅ ያስፈልጋል። ነገር ግን የሕዝቡን ብዛት ብቻ የሚያመለክት መረጃ መሰብሰብ በትምህርት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ሕጻናት ወይም በሥራ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ጎልማሳዎች ብዛት ለማወቅ ስለሕዝብ ተጨማሪ ማግኘት ያስፈልጋል። ስለዚህ በተለያዩ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ሰዎች ብዛት ለማወቅ በቆጠራው ጊዜ የግለሰቦች ዕድሜም ይጠየቃል። ከዚህም በላይ ለሕብረተሰቡ ኑሮ መሻሻልና ለኢኮኖሚው ልማት ለሚተለሙት ፕሮጀክቶች ሁሉ የሕዝቡን ብዛት ማወቅ ብቻ በቂ ስላልሆነ በተጨማሪ የሕዝቡን ልዩ ልዩ የስነ-ህዝብ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት የሚያመለክቱ እንደ ጾታ፣ ኃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ብሔረሰብ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፍልሰት ሁኔታ፣ የትምህርት ሁኔታ፣ የሥራ ሁኔታ፣ የተወለዱ ልጆች ብዛት፣ የሞቱ ሰዎች ብዛት፣ ....ወዘተ መረጃዎች በሕዝብና ቤት ቆጠራ ይሰበሰባሉ።

28. በኢትዮጵያ በ1999 ሊካሄድ የታቀደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያበረክት ማመን ተገቢ ነው። ለሐገሪቱ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት ዕቅድ ለማዘጋጀት እንዲሁም ለአስተዳደር ጉዳዮች ከሕዝብና ቤት ቆጠራው ውጤት የሚገኘው መረጃ መሠረታዊ መነሻ ይሆናል።

29. በአገሪቱ ያለውን የሕዝብ ብዛትና ሥርጭት ሁኔታ ማለትም በየትኛው ሥፍራ ምን ያህል ሕዝብ እንደሚኖር የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ መንግሥት የአስተዳደር ክልሎችን በሚገባ እንዲያደራጅ ያግዛል፡፡ ይህም ሕዝባዊ አገልግሎቶችን ለምሳሌ ትምህርት ቤቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ መንገዶችን፣ የውሃ ልማትን፣ ...ወዘተ ለማስፋፋት ጠቃሚ ነው፡፡ በተጨማሪም ከቆጠራው ሥራ የሚገኘው መረጃ ከሚሰጣቸው ጥቅሞች መካከል ለህዝባዊ ምርጫ ዕቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም የሚሰጠው አገልግሎት አንዱ ነው፡፡

30. ድርቅና ረሃብ የሚያጠቃቸውን አካባቢዎች ለወደፊት ዘለቄታነት ባለው መንገድ ለማቋቋምና ለችግሩ መፍትሄ ለማስገኘት የሕዝቡ ጂኦግራፊያዊ ስርጭት በሚገባ መታወቅ አለበት፡፡ ከዚህም በላይ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን በመላ ሃገሪቱ ለማከሄድ የሕዝቡን ብዛት፣ ስርጭት እና አጠቃላይ ጥንቅር የሚያመለክቱ መረጃዎች በመስረታዊነት ስለሚያስፈልጉ በዚህ ረገድ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

31. የሕዝብና ቤት ቆጠራው የሃገሪቱን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች ለማጥናትና ለመመዘን ከዚያም የእነዚህኑ አቋም ለማጠናከርና ለማሻሻል በሚያስችሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ ይረዳል፡፡ ይህም የሠራተኛ ቅጥር ጥያቄና የሰው ጉልበትን የማደራጀት ፕሮግራሞችን ለመቀየስ፣ ስለሕዝብ ፍልሰት፣ ስለቤቶች ሁኔታ፣ ስለትምህርት፣ ስለአካል ጉዳተኝነት፣...ወዘተ የተለያዩ የልማት ዕቅዶችን ለማዘጋጀት እንደዚሁም ሌሎች ለነዋሪው የሚጠቅሙ በርካታ ጉዳዮችን በሚገባ ለማከናወን ይረዳል፡፡ በመሆኑም ሕዝቡን በሚመለከት ትክክለኛና አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎች መሰብሰብ አስፈላጊ ነው፡፡

32. በሕዝብና ቤት ቆጠራው ተግባር የሚሰበሰበው መረጃ ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን፣ የሕዝብ ብዛትና ዕድገት ለማስላት፣ የሕዝቡን ስርጭትና የሕዝቡን በፆታና በዕድሜ አመዳደብ በሚመለከት ትንተናና ግምገማ ለማካሄድ ይረዳል፡፡ እንዲሁም የከተሞች ዕድገትና የጂኦግራፊያዊ ስርጭት፣ የሕዝቡን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ባሕሪያት የሚያመለክቱ መረጃዎች እንደ ፆታና ዕድሜ፣ የሥራ ሁኔታና የትምህርት ደረጃ፣ በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ስለአለው የልደትና የሞት ልዩነት፣ ለምርምርና ለጥናት፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ለማዘጋጀትና እንዲሁም የንግድንና የአገልግሎት ዕድገት በተመለከተ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ ለማቀድና በሚገባ ለመምራት ዓይነተኛ መሣሪያ ይሆናል፡፡

34. ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኙ መረጃዎች ከሚሰጡት ጥቅሞች ሌላው እነዚህ መረጃዎች በንግድ፣ በኢንዱስትሪና በግብርና ለተሠማሩ ድርጅቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ተፈላጊ የሆኑ የንግድ ዕቃዎችንና ሸቀጣሸቀጦችን ገምቶ ለተለያዩ ሸማቾች ለማቅረብና ፍላጎታቸውንም

ለማርካት የሕዝቡን ብዛት በዕድሜና በጾታ እንዲሁም የሥርጭት ሁኔታ በቅድሚያ ለማወቅ ይረዳል:: በተጨማሪም የንግድ ድርጅቶችንና እንዱስትሪዎችን ለማቋቋም በቅድሚያ የሰው ኃይል አቅርቦትን፣ እንደ መንገድ የመሳሰሉትን የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ... ወዘተ ለማቀድና ለማካሄድ ይጠቅማል::

34. በሕዝብና ቤት ቆጠራው አማካይነት የሚሰበሰቡት መረጃዎች ወደፊት በናሙና በአገር አቀፍ፣ በክልል መስተዳድር እና ከዚህ በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ደረጃ ለሚካሄዱ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጥናቶችን ለማከናወን እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ለግብርናና የመሳሰሉትን ለማከናወን የሚያስችል ዝርዝር (Frame) ለማስገኘት ያገለግላል::

35. ከሕዝብና ቤት ቆጠራው የሚገኙት መረጃዎች ለሃገሪቱ ከፍተኛ ጥቅም ከመስጠታቸውም በላይ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚፈለጉ የስነ-ህዝብ መረጃዎች ጥንቅር ጠቃሚ ናቸው::

36. በቆጠራ የሚገኘው መረጃ ቤቶችን በተመለከተ ወቅታዊና አስተማማኝ የሆነ የቤቶችን ብዛትና ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎችን በገጠር፣ በከተማ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና እንዲሁም በቀበሌ የአስተዳደር እርከኖች ለማግኘት ያስችላል::

### ለ. በቆጠራው የሚሠማራው የሰው ኃይል ብዛት

37. በ1999 ዓ.ም. በሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ 90,000 ያህል ቆጣሪዎች፣ 18,000 ተቆጣጣሪዎች እንዲሁም 3,000 የሚሆኑ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የቆጠራ ጽ/ቤት ሠራተኞች በድምሩ ወደ 111,000 የሚሆኑ ሠራተኞች ይሳተፋሉ ተብሎ ይገመታል::

### መ. በቆጠራው የሚሸፍነው አካባቢ

38. ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በመሠረቱ ቆጠራው በሚካሄድበት አገር ያለውን ሕዝብና ቤት መሉ በሙሉ መሸፈን አለበት:: በመሆኑም በ1999 የሚካሄደው ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ ፌዴራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኙትን ሁሉንም አካባቢዎች በመሸፈን በግንቦት ወር 1999 ለማካሄድ ታቅዷል:: ሆኖም የአፋርና የሱማሌ ክልሎች ሕዝቡ በሙሉ በቄየው የሚገኝበት (ለከብቶቻቸው ሳርና ውሃ ፍለጋ ሄደው የሚመለሱበት) ወቅት ያገናዘበ መሆን ስላለበት በህዳር ወር 2000 ዓ.ም. እንዲካሄድ ዕቅድ ተይዟል::

### ሠ. ቆጠራውን የሚያካሄደው ማን ነው?

39. በአዋጅ ቁጥር 449/1997 አንቀጽ 5 ለማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ኤጀንሲው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ጽ/ቤት ሆኖ በአገር አቀፍ ደረጃ የቆጠራውን የዕለት ተዕለት ሥራ ያስተባብራል:: ሆኖም የሕዝብና ቤት ቆጠራን የማካሄድ ተግባር በጣም ግዙፍና ከባድ እንዲሁም ከፍተኛ ወጪንና ብዛት ያለው የሰው ኃይል ስምሪት የሚያስፈልገው ሥራ ከመሆኑ የተነሣና ይህንን ተግባር ለማስፈጸም የተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችን፣ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን፣ ... ወዘተ ከፍተኛ ተሳትፎና ትብብር የሚጠይቅ ስለሆነ የቆጠራው ሥራ የሚካሄደው በዚሁ አዋጅ በተቋቋመ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ነው:: የተቋቋመው ኮሚሽን ከቆጠራ ሥራ አግባብነት ያላቸው የፌዴራልና የክልል አካላትን ያካተተ ነው::

## IX. የሕዝብና ቤት ቆጠራው ሥራ መዋቅርና የተለያዩ ኮሚቴዎች አደረጃጀት

40. የሕዝብና ቤት ቆጠራውን ዕቅድ ማውጣት፣ ማደራጀትና የቆጠራውንም ተግባር ከግቡ ለማድረስ ከፍ ያለ ብሄራዊ ድጋፍን የሚጠይቅ ነው:: በመሆኑም የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቶችና አንዳንድ ድርጅቶች ሙሉ ድጋፋቸውንና ትብብራቸውን ማበርከት ይኖርባቸዋል:: ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ መሠረት የተለየዩና አግባብ ያላቸው ሚ/ር መ/ቤቶችንና የክልል መንግስታት መሪዎችን ያቀፈና በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ተቋቁሟል:: በተዋረድም በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽኖች ይቋቋማሉ:: ከወረዳ በታችም በገጠርና በከተማ ቀበሌ አስተዳደሮች ደረጃም የሕዝብና ቤት ቆጠራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ:: እነኚህ በተዋረድ የተቋቋሙት /የሚቋቋሙት ኮሚሽኖች የቆጠራውን የዕለት ተዕለት ተግባራት የሚያከናውኑ ጽ/ቤት ይኖራቸዋል:: በማዕከል ደረጃ ለተቋቋመው ኮሚሽን የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ሆኖ እያገለገለ የሚገኝ ሲሆን በሁሉም ክልሎች እና ከዚያም በዞንና በወረዳ ደረጃ የህዝብና ቤት ቆጠራ ጽ/ቤቶች ይከፈታሉ:: ለእያንዳንዱ የህዝብና ቤት ቆጠራ ጽ/ቤት ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የጽ/ቤት ኃላፊና የቴክኒክ ኃላፊ ይመደባል::

41. በየደረጃው የተዋቀሩት ኮሚሽኖች፣ ጽ/ቤቶችና ኮሚቴዎች ቆጠራውን ለማስፈጸም በየደረጃው የቆጠራው ሥራ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት፣ አመራር በመስጠትና እንደአስፈላጊነቱ እርምጃ በመውሰድ ስለቆጠራው አፈጻጸም የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና ቆጠራው በታቀደው ጊዜ መመሪያን ተከትሎ መፈጸሙን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ይጠበቃል::

42. በክልል በዞንና በወረዳ የሚቋቋሙት የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽኖች የቆጠራውን ተግባር በአግባቡና በተቀናጀ ሁኔታ ለማከናወን እንዲችሉ የተለያዩ አጋዥ ኮሚቴዎች በስራቸው እንደአስፈላጊነቱ ይሰየማሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ነው፡፡

43. ለቆጠራው የሚያስፈልገው ቅድመ ዝግጅት በወቅቱና በተቀናጀ ሁኔታ ለማከናወንና የቆጠራውን ሥራ ዳር ለማድረስ ኃላፊነት የተጣለበት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በማዕከል የሚገኙ ባለሙያዎችና ኃላፊዎችን በሚከተለው ሁኔታ በተለያዩ ኮሚቴዎች አደራጅቶ ስራውን እያከናወነ ይገኛል፡፡

- *የቆጠራ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፡- የቆጠራ ሥራ ዝግጅትን ዕለት በዕለት ይከታተላል፡፡*
- *የቴክኒክ ኮሚቴ፡- የቆጠራ መጠይቆች፣ ቅጾች፣ መመሪያዎች ወዘተ ... የመሳሰሉትን ያዘጋጃል፡፡ በተጨማሪም በቴክኒክ ጉዳዮች ላይ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡*
- *የሎጅስቲክ ኮሚቴ፡- ለቆጠራው አስፈላጊ የሆኑት ዕቃዎችና ማጓጓዣን ያደራጃል፣ ያጓጉዛል፡፡*
- *የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ፡- በ1999 የሚካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ ከመንግስትና ከህዝብ በቂ ድጋፍና ትብብር እንዲያገኝ የትምህርትና ቅስቀሳ ተግባር ያከናውናል፡፡*
- *የድርጅታዊ መዋቅር ኮሚቴ፡- ለቆጠራው ተግባር አመቺ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር እና ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ያዘጋጃል፡፡*

## X. *የሕዝብና ቤት ቆጠራውን ለማካሄድ መከናወን ያለባቸው አበይት ቅድመ ዝግጅቶች*

### *ሀ. የቆጠራዉ ዕቅድ ዝግጅት*

44. ካለፉት ሁለት ቆጠራዎች ልምድ በመነሳትና በአሁኑ ቆጠራ ወቅት የሚኖሩትን ሁኔታዎች በማገናዘብ ቆጠራውን ለማካሄድ የሚያስችል ዕቅድ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ አዘጋጅቶ ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አቅርቧል፡፡ የቆጠራው ዕቅድ ሰነድ ይዘት የቆጠራው ዓላማና ጥቅም ቆጠራውን ለማካሄድ መከናወን ያለባቸው የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ተግባሮች ዝርዝር፣ የቆጠራው አፈጻጸም፣ በቆጠራው የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚጠናቀሩበትን ዘዴ፣ ቆጠራውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና የበጀት ፍላጎት ያጠቃልላል፡፡

## ለ. የቆጠራው የጊዜ ሰሌዳ

45. ለቆጠራው ዝግጅት ቆጠራው የሚካሄድባት፣ መረጃው የሚቀነባበርበትና ለሪፖርት የሚዘጋጅበት ጊዜ አስቀድሞ መወሰን ያለበት ስለሆነ ይኸው ተዘጋጅቶ ይገኛል። ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በዕዝል ተያይዞ ቀርቧል።

## ሐ. የውጭ ዕርዳታ ስለማግኘት

46. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማከሄድ በጣም ግዙፍ ተግባር በመሆኑ ለቆጠራው ተግባር ማስፈጸሚያ ከመንግሥት ከሚመደበው በጀት በተጨማሪ የውጪ ዕርዳታም ስለሚያስፈግ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የፕሮጀክት ሰነድ አዘጋጅቶ ከተለያዩ ለጋሽ ተቋማትና የልማት አጋሮች ጋር ተገቢዉን ግንኙነት በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህ ረገድ እስከ አሁን ድረስ በተደረገዉ ጥረት የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮገራም (UNDP) ለስካነር መሣሪያ (Scanner) መግዣና ለተለያዩ ሥልጠናዎች የሚዉል 2.3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የመደበ ሲሆን የተባበሩት መንግስታት የሕዝብ ጉዳይ ፈንድ (UNFPA) ደግሞ ለ5ኛዉ ሃገር አቀፍ የስነ ህዝብ መርሃ ግብር ከያዘዉ በጀት ለቆጠራዉ ቅድመ ዝግጅት ሥራና ለዋናዉ የቆጠራ ሥራ የሚዉል 1.9 ሚሊዮን የአሜሪከን ዶላር መድቧል። ከዚህ በተጨማሪም ከሌሎች ለጋሽ ተቋማትና የልማት አጋሮችን ድጋፍ ለማግኘት አስፈላጊው ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል።

## መ. የቆጠራ ካርታ ሥራ

47. ማንኛውም ሰው ወይም ቤት ሳይቆጠር እንዳይቀር እንደዚሁም ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይቆጠር ለማድረግ ቆጠራው ከመከናወኑ በፊት የቆጠራ ቦታና የመቆጠጠሪያ ቦታ ካርታዎች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ይህንንም ለማከናወን እያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ በገጠር ከ150-200 የሚደርሱ ቤተሰቦችን፣ በከተማ ደግሞ ከ150-200 የሚደርሱ ቤቶችን ያካተተ አካባቢን በማካለል ካርታዎች ይዘጋጃሉ። በዚህ መንገድ የተዘጋጀዉ ቦታ የቆጠራ ቦታ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ይህንኑ ከልሎ የሚያሳይ የቆጠራ ቦታ ካርታና መግለጫ ተዘጋጅቷል። የቆጠራ ቦታ ካርታ ማዘጋጀት ከላይ ከተጠቀሰው ዓላማ በተጨማሪ በቆጠራው የሚሰማራውን የሰው ኃይል/የቆጣሪዎችንና የተቆጣጣሪዎችን/ ብዛት ለመገመት፣ ወደፊት በአገሪቱ ለሚካሄዱ የናሙና ጥናቶች ዝግጅት መሠረት የሚሆን ዝርዝር (Frame) ለማስገኘት፣ ...ወዘተ ጥቅሞች ይኖሩታል።

48. ከአራት እስከ አምስት የሚሆኑ ተዋሳኝ የቆጠራ ቦታዎችም እንደ አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ ተወስደው የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ ተዘጋጅቶላቸዋል። በዚህ ዓይነት አገሪቱን በሙሉ ከተማውንና ገጠሩን ጭምር በቆጠራ ቦታዎችና በመቆጣጠሪያ ቦታዎች በመሸንሸን የሕዝብና

ቤት ቆጠራ ካርታ ሥራ ተከናውኗል። በቆጠራውም ወቅት አንድ ቆጣሪ በአንድ የቆጠራ ቦታ ተመድቦ የቆጠራውን ተግባር እንዲያከናውን ይደረጋል። እንዲሁም አንድ ተቆጣጣሪ እስከ ሰባት የሚደርሱ ቆጣሪዎችን በአንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ በማሠማራትና ሥራውን በመቆጣጠር የቆጠራውን ተግባር ያስፈጽማል።

49. የቆጠራ ካርታ ሥራውን ለማስፈጸም ከነሃሴ 1995 ተጀምሮ ሲከናወን የቆዩ ሲሆን በየጊዜው የቆጠራ ካርታ ሥራ ቡድኖችን በመጨመር እስከ 130 ቡድኖችና (እያንዳንዱ ቡድን 6 ረዳት ካርታ ሠራተኞችና 1 ፕሮፌሽናል ተቆጣጣሪ የያዘ) ተሠማርተው የቆጠራ ካርታ ሥራውን ሲያከናውኑ ቆይተዋል።

50. የካርታው ሥራ ቡድኑ የተመደበበት ወረዳ እንደደረሰ ስለካርታው ሥራ ዓላማና ጥቅም በማስረዳት ከሚመለከታቸው የወረዳ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር በወረዳው ውስጥ ያሉትን የገጠርና የከተማ ቀበሌዎችን ስምና የሊቃነ መናብርት ስም መረጃ መዝግቦ በመያዝ በየቀበሌው በመገኘት በአመራር አካላት በሚመደብለት መንገድ መሪ በመመራት የቀበሌዎችን ድንበር በመለየትና የቤቶችና የቤተሰቦች ምዝገባ በማካሄድ ሥራውን ያከናውናል።

51. የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚዘጋጀው አሁን በሥራ ላይ ያለውን የቀበሌ/የወረዳ ድንበር መነሻ በማድረግ ሲሆን ክልሎች በውስጣቸው ወይም ከአጐራባች ክልል ጋር ተስማምተው የድንበር ለውጥ ቢያደርጉ ካርታውና በካርታው ላይ ተመስርቶ የተገኘው የቆጠራ ውጤት በዚሁ መሠረት ይስተካከላል። በአጠቃላይ የቆጠራ ካርታ የሚሰራው የቆጠራውን ስራ በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ታስቦ የተዘጋጀ ነው እንጂ ለአስተዳደር ድንበር መነሻ/ማስረጃ እንዲውል አይደለም።

52. የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው እስከ ህዳር 30 ወር 1999 ከጋምቤላ፣ አፋርና ሶማሌ ከተወሰኑ ወረዳዎች በስተቀር ከሞላ ጐደል ተጠናቋል።

53. የመስክ ሥራውን ሂደትና ጥራት ለመቆጣጠርና ለመገምገም በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች፣ የካርታ ሥራ ቴክኒክ ኮሚቴና ሥራው በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝትና የቁጥጥር ሥራዎች ተካሂደዋል። አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ችግሮች ሲከሰቱ በወቅቱ በሥፍራው ተገኝቶ ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች ሥራው በመመሪያው መሠረት እንዲከናወን ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል።

### ሠ. የመጠይቆችና መመሪያዎች ዝግጅትና ህትመት

54. የመጠይቆችና የመመሪያዎች ዝግጅት ተግባር በቆጠራው ወቅት የሕዝብና ቤት መረጃዎች የሚሰበሰብባቸዉን መጠይቆች ማዘጋጀት፣ የመጠይቆቹን አሞላል የሚያስረዱ የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ቅጾችንና መመሪያዎችን /የህዝብና ቤት ቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊዎች መመሪያ፣ የፋይናንስና አስተዳደር መመሪያ፣ ... ወዘተ/ ማዘጋጀትንና ያካትታል:: በመሆኑም በ1999 ዓ.ም. ለሚከናወነዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት በሙሉ ተከናዉነዋል:: በሌላ በኩል በ1999 ዓ.ም የሚከናወነዉን ሀገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የስካኒንግ ቴክኖሎጂ "Scanning Technology" በመጠቀም ለመሥራት በተወሰነው መሠረት ለቆጠራ ሥራዉ የሚያስፈልጉ መጠይቆችና መመሪያዎች ለዚሁ በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተዋል:: እነዚህም መመሪያዎች፣ ቅጾችና መጠይቆች የስካኒንግ ቴክኖሎጂን መጠቀም ሊያመች በሚያስችል መንገድ ተደርገው ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው እንዲታተሙ ተደርጓል::

### ረ. ልዩ ዝግጅት የሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ቆጠራ

### መጠለያ ቤት የሌላቸው ነዋሪዎች ቆጠራ

55. መጠለያ ቤት የሌላቸው ነዋሪዎች በቆጠራው መሸፈን ስለሚኖርባቸው ግለሰቦቹ በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚያድሩባቸው ቦታዎች የቤቶችና ቤተሰቦች ምዝገባ በሚካሄድበት ጊዜና በቆጠራው ወቅትም በሙሉ በትክክል ተለይተው እንዲታወቁ ይደረጋል:: መጠለያ ቤት የሌላቸው ነዋሪዎች የሚያድሩበትን ቦታ በመለየቱ ተግባር ላይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጉልህ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል:: በዚሁ መሠረት ቆጠራው የሚከናወነው በቆጠራው ወቅት በአንድ በሚወሰን ቀን ተመሳሳይና አመቺ ሠዓት በመምረጥ እያንዳንዱ ቆጣሪና ተቆጣጣሪ መጠለያ ቤት የሌላቸው ግለሰቦች የሚያድሩባቸው ቦታዎች ድረስ በመሄድ ነው:: በዚህም ወቅት ቆጠራው በፖሊስ ሠራዊት አባላት፣ ከቀበሌ ተመራጮች ትብብርና እርዳታ በማግኘት እንዲሁም ተገቢውን ገለፃ በማድረግና በማግባባት ስለእነሱ የተለያዩ መረጃዎችን በሚመለከተው መጠይቅ እንዲሰበሰብ ይደረጋል::

### የጋርዮሽ መኖሪያ ነዋሪዎች ቆጠራ

56. የጋርዮሽ መኖሪያ የሚባለው በዝምድና ያልተሳሰሩ /የተሳሰሩም ሊሆኑ ይችላሉ/ ከቤቱ የሚገኙ አገልግሎቶችን አብረው በመጋራት ሰዎች የሚኖሩባቸው ስፍራ ነው:: እነዚህም

ሆቴል/ሆስቴል፣ አዳሪ ት/ቤቶች፣ ህፃናት ማሳደጊያዎች፣ አረጋውያን መጦሪያዎች፣ ፀባይ ማረሚያዎች፣ የወታደር ካምፖች፣ አድባራት፣ የጋራ መኖሪያ የሠራተኛ ካምፖች፣ ወህኒ ቤቶች …ወዘተ ናቸው። እነዚህን በቆጠራ ካርታ ሥራ ወቅትና በቆጠራው ጊዜም የቤተሰቦችና ቤቶች ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅት በትክክል ለይቶ እንዲታወቁ በማድረግ በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ ለሚኖሩ ነዋሪዎች በሙሉ የሚመለከታቸው መረጃ በረጅም መጠይቅ እንዲሰበሰብላቸው ይደረጋል።

## የውጭ አገር ዜጎች ቆጠራ

57. የሕዝብና ቤት ቆጠራ በሀገሪቱ የሚገኙ የውጪ አገር ዜጎችን ጨምሮ መካሄድ ይኖርበታል። በአዲስ አበባ የሚኖሩ የውጪ አገር ዜጎችን በቆጠራው ለመሸፈን አጭሩ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቅ አስቀድሞ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን ይህ መጠይቅ በቀጥታ ለግለሰቦቹ ተሰጥቷቸው እራሳቸው የሚሞሉት ይሆናል። በሌሎች የአገሪቱ ክፍል ለሚገኙ የውጪ አገር ዜጎች እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጎች በቆጠራው እንዲሸፈኑ ይደረጋል።

## የአርብቶ አደር አካባቢዎች ቆጠራ

58. በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማካሄድ ከዚህ ቀደም የነበረውን ልምድ ለማሻሻል ጥናትና ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህም ይህንን ጥናት የሚያካሂድ የአርብቶ አደር አካባቢ የቆጠራ አሠራር ኮሚቴ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ደረጃ ተቋቁሞ የአርብቶ አደሩን ሕዝብ መቁጠር የሚቻልበትን መንገድ እያጠና ሲሆን ቆጠራውም በጥናቱ መሠረት በተወሰነው ጊዜ ይካሄዳል። በግንቦት ወር 1999 አብዛኛው አርብቶ አደር በመደበኛ መኖሪያ ቂየው ስለማይገኝ በዚህን ወቅት ለዚህ አካባቢ ለሌሎች የተመረጠው የቆጠራ ጊዜ አመቺ ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም ከጥናቱ በተገኘው መረጃና ከክልሎች ጋር በተደረገው ውይይት በሶማሌና አፋር ክልሎች ቆጠራው ህዳር ወር 2000 ዓ.ም. እንዲሆን ተወስኗል።

## ሰ. የሙከራ ቆጠራ ማካሄድ

59. የሙከራ ቆጠራ ተግባር አበይት ዓላማ በተወሰኑ አካባቢዎች ለዋናው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተዘጋጁ መጠይቆችንና ቅጾችን በመሙላት በአስተዳደር፣ በሎጀስቲክስ (ለመስክ ሠራተኞች ትራንስፖርት፣ መጠለያ፣ ምግብ …ወዘተ) በሰው ኃይል በተመለከተ የሚያጋጥሙትን ችግሮች መረዳትና ማወቅ እንዲሁም የተዘጋጁ መጠይቆችና መመሪያዎች ግልጽነት፣ የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ጥራት፣ …ወዘተ ለመገምገም ሲሆን ከዚያም በሙከራው ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን

አስቀድሞ በመለየት ለዋናው ቆጠራ መፍትሄዎችን መሻት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የመደበኛውን የቆጠራ አሠራር በመከተል የመጀመሪያው የሙከራ ቆጠራ በመላው አገሪቱ በናሙና በተመረጡ ገጠርና ከተማ ቀበሌዎች በሰኔ ወር 1998ዓ.ም ተካሄዷል፡፡ በተጨማሪም በ1999 ዓ.ም. ለሚካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ የስካኒንግ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለመስራት በተወሰነው መሠረት ለዚሁ የተዘጋጁ መጠይቆች፣ ቅጾችና መመሪያዎችን ለመፈተሽ በነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም ሁለተኛው የሙከራ ቆጠራ ተካሂዷል፡፡

60. ለሙከራ ቆጠራ ከሁሉም ክልሎች /ከአፋርና ሶማሌ ክልሎች በስተቀር/ በናሙናነት የተመረጡት 250 የቆጠራ ቦታዎች ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ 150 የቆጠራ ቦታዎች በመደበኛው የሙከራ ቆጠራ አሠራር የተካሄደባቸውና በቀሪዎቹ 100 የቆጠራ ቦታዎች ደግሞ በዓይነቱ የመጀመሪያ አሠራር የሆነው የስካኒንግ ዘዴ ተካሂዶባቸዋል፡፡ የቆጠራ ቦታዎች አመራረጥም የሕዝብ አሠፋፈር ጥግግትን፣ የቆጠራ ቦታው ከዋናው መንገድ ያለውን ርቀት፣ የመሬቱ አቀማመጥ /ወጣ ገባ ወይስ ሜዳማ/፣ በቆጠራ ጊዜ ያለውን የዝናብ ሁኔታንና የነዋሪዎቹን የቋንቋ ስብጥር ሁኔታን በአጠቃላይ በዋናው ቆጠራ ያጋጥማሉ ተብሎ የሚታሰቡ ችግሮችን የሚያንፀባርቁ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር፡፡ ከ250 የቆጠራ ቦታዎች መካከል 48 የከተማ ቆጠራ ቦታዎች ሲሆኑ 202 ደግሞ የገጠር ቆጠራ ቦታዎች ናቸው፡፡

61. በመደበኛ የሙከራ ቆጠራው ወደ 43,000 ቤተሰቦች የተሸፈኑ መሆኑ የተገመተ ሲሆን ቆጣሪዎችን በማሰልጠን፣ መጠይቆችን በማረምና በማሻሻል፣ በቆጣሪዎችና በተቆጣጣሪዎች መመሪያዎች ውስጥ የታዩ ግድፈቶች ሊሻሻሉ የሚገባቸው መመሪያዎችን በማረም፣ መጠይቆችን ለመሙላት የሚወስደውን ጊዜ በማወቅና ሌሎችም በዋናው ቆጠራ ወቅት ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ነገሮች በማወቅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ሊሻሻሉ ወይም ሊስተካከሉ የሚገባቸው ሁሉ ተሻሽለውና ተስተካክለው ለዋናው ቆጠራ ተዘጋጅተዋል፡፡

## ሸ. በቆጠራው የሚሠማሩ ሠራተኞችን ምልመላ፣ ስልጠናና ምደባ

62. በአስልጣኝነት ላይ የሚሣተፉ የሁለተኛ ደረጃ መምህራንን እንዲሁም በተቆጣጣሪነትና በቆጣሪነት የሚመደቡ የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራን ከአገር አቀፉ የኮሚሽን ጽ/ቤት በሚተላለፈው አንድ ወጥ የሆነ መመዘኛ መሠረት ብቁ የሆኑት በየደረጃው ባሉ የኮሚሽኑ ጽ/ቤቶችና የትምህርት ቢሮዎች አማካኝነት እንዲመለመሉ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም የተመለመሉና በቆጠራው የሚሰማሩ ሠራተኞችን ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ሥልጠናውም የሚሰጠው በመጀመሪያው ዙር በቆጠራው የሚሠማሩ

ባለሙያዎችን ለሚያሰለጥኑ ባለሙያዎች፣ ከዚያም በሁለተኛው ዙር በየአስተዳደር ክልሎች በቆጠራው ለሚሠማሩ የቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ በሦስተኛ ዙር ደግሞ ለተቆጣጣሪዎችና ለቆጣሪዎች በስፋት ይሰጣል::

63. ከላይ በተጠቀሰው መሠረት በቆጠራው ሥራ ለሚሠማራው የሰው ኃይል በሦስት ዙር የተከፈለ ሥልጠና ለመስጠት ዕቅድ ወጥቷል:: በዚህ መሠረት:-

ሀ. በመጀመሪያ ዙር ስልጠና ማለትም በአሠልጣኞች ሥልጠና የሚሣተፉ ወደ 300 የሚደርሱ ፕሮፌሽናልና መለስተኛ ፕሮፌሽናል የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ባልደረቦች በዋናው መ/ቤት የ10 ቀናት ሥልጠና በመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም ይሰጣል::

ለ. በሁለተኛ ዙር ወደ 4,745 ለሚደርሱ አሰልጣኞች በክልልና በዞን ደረጃ ሥልጠና እንደሚሰጥ ታቅዷል:: በመሆኑም ወደ 2,487 ለሚደርሱ በኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚገኙ የመስክ ሠራተኞችና ተቆጣጣሪዎች በሚያዝያ ወር 1999 ዓ.ም የሚሰጥ ሲሆን በተመሣሣይ ደረጃ ለተቀሩት 2,258 ለሚደርሱ ከሌላ መስሪያ ቤት ለሚመጡ ባለሙያዎች ደግሞ በዚሁ ወር 1999 ዓ.ም በየክልሉና በየዞኑ የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል::

ሐ. በሦስተኛ ዙር በዋናው ቆጠራ ሥራ ላይ የሚሠማሩ ቆጣሪ መምህራን ወደ 91286 ለሚደርሱ ቆጣሪዎች ይሰለጥናሉ ማለት ነው:: እንዲሁም እነዚህን ቆጣሪዎች የሚቆጣጠሩ ወደ 17,388 የሚደርሱ ተቆጣጣሪ መምህራን አብሮ ስልጠናው ይከናወናል:: በመጨረሻም ስልጠናውን የወሰዱ የመስክ ሠራተኞችን መደልደልና ወደ ምድብ የቆጠራ ቦታና መቆጣጠሪያ ቦታ እንዲሠማሩ ይደረጋል::

64. በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዙር በአሠልጣኝነት የሠለጠኑ የኤጀንሲው መ/ቤት ፕሮፌሽናልና መለስተኛ ፕሮፌሽናል እንዲሁም የመስክ ሠራተኞች በቆጠራው ለሚሠማሩ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች አሠልጣኝ ከመሆናቸውም በላይ በክልል፣ በዞንና በወረዳ በመመደብ የጽ/ቤት ኃላፊዎች በመሆን የቆጠራውን ሥራ ያስፈፅማሉ::

### ቀ. የቆጠራ ዶክሜንቶችን፣ መጠይቆችንና የተለያዩ መመሪያዎችን ማደራጀትና ወደ መስክ መላክ

65. በ1999 ለሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚያገለግሉ የቆጠራ ዶክሜንቶችን፣ መጠይቆችንና መመሪያዎችን ማዘጋጀት የቆጠራው የቅድመ ዝግጅት ሥራ ከሚያካትታቸው ተግባራት መካከል አንዱና ዋነኛው ሲሆን በተለይ እነዚህን በቁጥር እጅግ ብዙ የሆኑትን የቆጠራ

ዶክሜንቶች፣ መጠይቆችና መመሪያዎች በሚፈለገው መጠንና አይነት የማደራጀትና ወደ መስክ የማሰራጨቱ ሥራ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ የሚጠይቅና በተቀናጀ መልኩ መከናወን ያለበት ጉዳይ ነው። ይህንን ግዙፍ ተግባር በተቀናጀ መልኩ ለማከናወን ይቻል ዘንድ በዋናው መ/ቤት የሎጂስቲክ ኮሚቴ ተቋቁሞ ተገቢውን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህ ኮሚቴ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ለቆጠራው ተግባር የሚያገለግሉ የቆጠራ ዶክሜንቶችን፣ መጠይቆችን፣ የተለያዩ መመሪያዎችንና የሥራ መሣሪያዎችን በሚፈለገው መጠንና ዓይነት የማደራጀት፣ በእያንዳንዱ ቆጣሪና ተቆጣጣሪ ቦርሳ ውስጥ የማስገባትና ወደ መስክ ማሰራጨት ይገኙበታል። የሥርጭቱ ተግባር በመላው ሀገሪቱ የሚካሄድ ሰፊ ሥራ በመሆኑ የተለያዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ... ወዘተ የሚሣተፉበት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

### በ. የመረጃ ቅንብር ዝግጅት

66. የ1999 ዓ.ም. የህዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በስካኒንግ የመረጃ ቅበላ ዘዴ የሚከናወን በመሆኑ በቆጠራው ከመስክ የሚሰበሰበው መረጃ በቀጥታ ወደ ስካኒንግ መሣሪያው በማስገባት እንዲቀነባበር ይደረጋል። በመጨረሻም በኮምፒዩተር ለማጠናቀር አስፈላጊ ሠንጠረዦችና የኮምፒዩተር ፕሮግራሞች ዝግጅት እየተካሄደ ይገኛል። ከመስክ የተሰበሰበው መረጃ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጁ ፕሮግራሞችን በመጠቀም ከተጠናቀረ በኋላ ለመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ትንተና እና ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ትንተና ዝግጅት ይደረጋል።

## XI. *በቆጠራው የሚሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነት*

67. በግንቦት 1999 ሊካሄድ በታቀደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በገጠርና በከተማ በአብዛኛው ተመሳሳይ መረጃዎችን ይሰበሰባሉ። ቢሆንም የቤት መረጃን አስመልክቶ በገጠርና በከተማ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለማንፀባረቅና ለማነጻጸር እንዲያስችል በገጠርና በከተማ የሚጠየቁ ተመሳሳይ ጥያቄዎች በቆጠራው መጠይቅ እንዲካተቱ ተደርጓል። ቆጠራው ከቤት ቤት በመሄድና በመዘዋወር ሰፋ ያለ መረጃ የሚሰብሰብበት ብዙ ወጪና ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑ ሁለት ዓይነት መጠይቆች (አጭር ና ረዥም) ተዘጋጅተዋል። አጭር መጠይቅ በመጠቀም የተወሰኑ ተመሳሳይ መረጃዎች ከሁሉም ቤተሰቦች የሚሰበሰቡ ሲሆን ዝርዝር መረጃዎች ደግሞ ረዥም መጠይቅ በመጠቀም በናሙና ከተመረጡ ቤተሰቦች ከቤት ቤት በመሄድ ይሰበሰባሉ።

68\. *ከሁሉም ቤተሰቦች አጭር መጠይቅ በመጠቀም የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡-*

1. የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም
2. የነዋሪነትና አኗኗር ሁኔታ
3. ከቤተሰብ ሃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና
4. ጾታ
5. ዕድሜ
6. ሃይማኖት
7. የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣
8. የብሔር/ብሔረሰብ ሁኔታ
9. የአካል ጉዳተኝነትና የአእምሮ መታወክ ሁኔታ፤የጉዳቱ/የችግሩ ዓይነት፤
10. የወላጅ አልባ ህፃናት ሁኔታ(ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት)

69\. *በናሙና ከተመረጡ ቤተሰቦች ረዥም መጠይቅ በመጠቀም የሚሰበሰቡ መረጃዎች፡-*

1. የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም
2. የነዋሪነትና የአኗኗር ሁኔታ
3. ከቤተሰብ ሃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና
4. ጾታ
5. ዕድሜ
6. ሃይማኖት
7. የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣
8. የብሔር/ብሔረሰብ ሁኔታ
9. የአካል ጉዳተኛነት ሁኔታ
   - 9.1 የማየት፣ የመስማት፣ የመናገር፣ ወይም የመቆም የመራመድ/ የመቀመጥ የሰውነት አካል መንቀሳቀስ ችግር የእጅ ወይም የእግር ለመሥራት ችግር ያለባቸው ወይም የአእምሮ ዘገምተኝነት የአእምሮ መታወክ ወይም ሌላ የአእምሮ/ የአካል ጉዳት
   - 9.2 የጉዳቱ / የችግሩ ዓይነት
   - 9.3 የጉዳቱ / የችግሩ መንስኤ/ ምክንያት
10. የፍልሰት ሁኔታ
    - 10.1 በከተማ/ ወረዳ ገጠር ክፍል ውስጥ ያለማቋረጥ የኖሩበት ዓመት
    - 10.2 ቀድሞ ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ ከተማ ወይም ገጠር ስለመሆኑና፣ የሚገኝበት ዞን
11. የወላጅ አልባ ህፃናት ሁኔታ(ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት)

ዶክሜንቶች፣ መጠይቆችና መመሪያዎች በሚፈለገው መጠንና አይነት የማደራጀትና ወደ መስክ የማስራጨቱ ሥራ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ የሚጠይቅና በተቀናጀ መልኩ መከናወን ያለበት ጉዳይ ነው። ይህንን ግዙፍ ተግባር በተቀናጀ መልኩ ለማከናወን ይቻል ዘንድ በዋናው መ/ቤት የሎጂስቲክ ኮሚቴ ተቋቁሞ ተገቢውን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህ ኮሚቴ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ለቆጠራው ተግባር የሚያገለግሉ የቆጠራ ዶክሜንቶችን፣ መጠይቆችን፣ የተለያዩ መመሪያዎችንና የሥራ መሣሪያዎችን በሚፈለገው መጠንና ዓይነት የማደራጀት፣ በእያንዳንዱ ቆጣሪና ተቆጣጣሪ ቦርሳ ውስጥ የማስገባትና ወደ መስክ ማሰራጨት ይገኙበታል። የሥርጭቱ ተግባር በመላው ሀገሪቱ የሚካሄድ ስፊ ሥራ በመሆኑ የተለያዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ... ወዘተ የሚሣተፉበት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

## በ. የመረጃ ቅንብር ዝግጅት

66. የ1999 ዓ.ም. የህዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በስካኒንግ የመረጃ ቅበላ ዘዴ የሚከናወን በመሆኑ በቆጠራው ከመስክ የሚሰበሰበው መረጃ በቀጥታ ወደ ስካኒንግ መሣሪያው በማስገባት እንዲቀነባበር ይደረጋል። በመጨረሻም በኮምፒዩተር ለማጠናቀር አስፈላጊ ሠንጠረዦችና የኮምፒዩተር ፕሮግራሞች ዝግጅት እየተካሄደ ይገኛል። ከመስክ የተሰበሰበው መረጃ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጁ ፕሮግራሞችን በመጠቀም ከተጠናቀረ በኋላ ለመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ትንተና እና ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ትንተና ዝግጅት ይደረጋል።

## XI. በቆጠራው የሚሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነት

67. በግንቦት 1999 ሲካሄድ በታቀደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በገጠርና በከተማ በአብዛኛው ተመሳሳይ መረጃዎችን ይሰበሰባሉ። ቢሆንም የቤት መረጃን አስመልክቶ በገጠርና በከተማ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለማንፀባረቅና ለማነጻጸር እንዲያስችል በገጠርና በከተማ የሚጠየቁ ተመሳሳይ ጥያቄዎች በቆጠራው መጠይቅ እንዲካተቱ ተደርጓል። ቆጠራው ከቤት ቤት በመሄድና በመዘዋወር ስፋ ያለ መረጃ የሚሰብሰብበት ብዙ ወጪና ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑ ሁለት ዓይነት መጠይቆች (አጭር ና ረዥም) ተዘጋጅተዋል። አጭር መጠይቅ በመጠቀም የተወሰኑ ተመሳሳይ መረጃዎች ከሁሉም ቤተሰቦች የሚሰበሰቡ ሲሆን ዝርዝር መረጃዎች ደግሞ ረዥም መጠይቅ በመጠቀም በናሙና ከተመረጡ ቤተሰቦች ከቤት ቤት በመሄድ ይሰበሰባሉ።

68. *ከሁሉም ቤተሰቦች አጭር መጠይቅ በመጠቀም የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡-*

1. የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም
2. የነዋሪነትና አኗኗር ሁኔታ
3. ከቤተሰብ ሃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና
4. ጾታ
5. ዕድሜ
6. ሃይማኖት
7. የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣
8. የብሔር/ብሔረሰብ ሁኔታ
9. የአካል ጉዳተኝነትና የአእምሮ መታወክ ሁኔታ፤የጉዳቱ/የችግሩ ዓይነት፤
10. የወላጅ አልባ ህፃናት ሁኔታ(ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት)

69. *በናሙና ከተመረጡ ቤተሰቦች ረዥም መጠይቅ በመጠቀም የሚሰበሰቡ መረጃዎች፡-*

1. የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም
2. የነዋሪነትና የአኗኗር ሁኔታ
3. ከቤተሰብ ሃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና
4. ጾታ
5. ዕድሜ
6. ሃይማኖት
7. የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣
8. የብሔር/ብሔረሰብ ሁኔታ
9. የአካል ጉዳተኛነት ሁኔታ
   9.1 የማየት፣ የመስማት፣ የመናገር፣ ወይም የመቆም የመራመድ/ የመቀመጥ የሰውነት አካል መንቀሳቀስ ችግር የእጅ ወይም የእግር ለመሥራት ችግር ያለባቸው ወይም የአእምሮ ዘገምተኝነት የአእምሮ መታወክ ወይም ሌላ የአእምሮ/ የአካል ጉዳት
   9.2 የጉዳቱ / የችግሩ ዓይነት
   9.3 የጉዳቱ / የችግሩ መንስኤ/ ምክንያት
10. የፍልሰት ሁኔታ
    10.1 በከተማ/ ወረዳ ገጠር ክፍል ውስጥ ያለማቋረጥ የኖሩበት ዓመት
    10.2 ቀድሞ ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ ከተማ ወይም ገጠር ስለመሆኑና፣ የሚገኝበት ዞን
11. የወላጅ አልባ ህፃናት ሁኔታ(ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት)

11.1 ወላጅ እናት በሕይወት ስለመኖር/አለመኖራቸው

11.2 ወላጅ አባት በሕይወት ስለመኖር/አለመኖራቸው

12. ትምህርት ሁኔታ

12.1 የማንበብና የመጻፍ ችሎታ

12.2 በመማር ላይ ያሉት ክፍል

12.3 ያጠናቀቁት ከፍተኛ ክፍል

13. የሥራ ሁኔታ

13.1 ባለፉት ሰባት ቀናት በምርታማ ሥራ መሳተፍ

13.2 በቀጣይ 1 ወር ሥራ ለመሥራት ያላቸው ዝግጅት

13.3 ባለፉት 12 ወራት በምርታማ ሥራ መሳተፍ

13.4 የቅጥር ሁኔታ

14. የጋብቻ ሁኔታ

15. የወሊድ ሁኔታ በሕይወት ዘመን ለወለድዋቸው ልጆች

15.1 በጠቅላላ በሕይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት

15.2 በሞት የተለዩ ወንዶችና ሴቶችልጆች ብዛት

15.3 ባለፉት 12 ወራት(ከግንቦት 21/1998 እስከ ግንቦት20/1999) በሕይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት

16. በቤተሰብ ውስጥ ስለተከሰተ ሞት

16.1 ከዓምና ግንቦት 1998 (ከግንቦት 21/1998 እስከ ግንቦት20/1999) ወዲህ ከቤተሰቡ ውስጥ የሞተ ሰው ብዛት

16.2 ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር የተያያዘ የሞት ሁኔታ

## 70. *ስለ ቤት (በገጠርና በከተማ) የሚሰበሰቡ መረጃዎች*

1. የቤቱ ዓይነት
2. ቤቱ ከተሠራ ስንት ዓመት እንደሆነው፣
3. የቤቱ ግድግዳ አብዛኛው ከምን እንደተሠራ፣
4. የቤቱ ጣሪያ አብዛኛው ከምን እንደተሠራ፣
5. የቤቱ ኮርኒስ አብዛኛው ከምን እንደተሠራ፣
6. የቤቱ ወለል አብዛኛው ከምን እንደተሠራ፣
7. የቤቱ ክፍሎች ብዛት፣
8. የቤቱ ይዞታ፣
9. የቤቱ ነዋሪዎች የመጠጥ ውሃ ከየት እንደሚያገኙ
10. ቤቱ ያለው የማድቤት ዓይነትና አጠቃቀም

11. ቤቱ ለምግብ ማብሰያ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው የማገዶ ዓይነት

12. ቤቱ ያለው የገላ መታጠቢያ ዓይነት

13. ቤቱ ያለው የመፀዳጃ አገልግሎት ዓይነትና አጠቃቀም

14. ቤቱ ያለው የመብራት አገልግሎት ዓይነት

15. በቤቱ/የሚሠራሬዲዮ ቴሌቪዥን መደበኛ/ሽቦ አልባ ስልክ መኖር አለመኖር (የሞባይል ስልክን አይጨምርም)

16. ደረቅ ቆሻሻ ከቤቱ እንዴት እንደሚወገድ

17. ቤተሰቡ በሚያድርበት ቤት ከብቶች ያድሩ እንደሆነ

## XII. በቆጠራው ወቅት የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታና የህብረተሰቡ ትብብር

### ሀ. መረጃውን የሚሰበስቡት እነማንናቸው?

71. የሕዝብና ቤት ቆጠራን በማካሔድ የሚገኙትን መረጃዎች የሚሰበስቡት ሠራተኞች ቆጣሪ/መረጃ ሰብሳቢ/ ይባላሉ:: ቆጣሪዎቹ ሴት ወይም ወንድ ሊሆኑ ይችላሉ:: እነዚህ ቆጣሪዎች በሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የተሠማሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ "ቆጣሪ" የሚል የሕዝብና ቤት ቆጠራ መታወቂያ ባጅ ይኖራቸዋል:: እነዚህ መረጃ ሰብሳቢዎች በግል ወደ እያንዳንዱ መረጃ ሰጪ ቤት በሚሄዱበት ጊዜ በትክክል ራሳቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ ባጃቸውን ስለሚይዙ ማንኛ ውም ሰው በነዚህ ማስረጃዎች አማካኝነት ቆጣሪ መሆናቸውን ለመለየት ይችላል:: እነዚህን መታወቂያዎች/መለያዎች ያልያዘ/ያልያዘች ቆጣሪ የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ሰብሳቢ ነኝ ቢል/ብትል እንኳን ህብረተሰቡ ሊቀበላቸው አይገባም:: ይልቁንም ህብረተሰቡ ጥርጣሬ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን ሲመለከት ቆጣሪዎቹ የደረት ባጃቸውን/ደብዳቤያቸውን እንዲያሳዩ የመጠየቅ፣ ለማሳየት ያልቻሉ ቆጣሪዎችን ወዲያው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል::

72. በሌላ በኩል ወደ አምስት/5/ የሚደርሱ ቆጣሪዎችን ሥራ የሚቆጣጠር/ የምትቆጣጠር ግለሰብ "ተቆጣጣሪ" ይባላል/ትባላለች:: በቆጣሪዎች ላይ እንደተደረገው ሁሉ በነዚህ ተቆጣጣሪዎች ላይም ጥርጣሬ ካለ መታወቂያቸውን ጠይቆ ተቆጣጣሪ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

73. በዚህ ሥራ የሚሠማሩ ቆጣሪዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ናቸው:: ነገር ግን ቆጠራው ከሚካሄድበት አካባቢ በቂ ቆጣሪ መምህራንን ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ

ከአቅራቢያው ከሚገኙ አካባቢዎች እንዲመለመሉ ይደረጋል:: ለዚህ ታላቅ ሀገራዊ ተግባር በተቆጣጣሪነት የሚሰማሩት ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ናቸው::

## ለ. መረጃዎች የሚሰበሰቡት እንዴት ነው?

74. የህዝብና ቤት መረጃ የሚሰበስቡ ቆጣሪዎች ከቆጠራው ቀን ጀምሮ በተመደቡበት የቆጠራ ቦታ በሚሰጣቸው የቆጠራ ቦታ ካርታ መሠረት ከቤት ወደ ቤት በመሄድ በመጀመሪያ የቤት የቤተሰብና የድርጅት ምዝገባ ያከናውናሉ:: ምዝገባው የሚያገለግለው በዚያ ቆጠራ ቦታ ክልል ውስጥ ያሉ ቤቶችና ቤተሰቦች ሳይደገሙ/ ሳይዘለሉ መቆጠራቸውን ለማረጋገጥ ነው:: ቆጣሪዎች ይህንን ሲያደርጉ በቤቱ በራፍ ላይ በሚታይ ቦታ በጠመኔ የቤቱን ተራ ቁጥር ይፅፋሉ :: ምዝገባው ከተጠናቀቀ በኋላ እነዚህ ቆጣሪዎች ምዝገባውን ባከናወኑ ሁኔታ ከቤት ወደ ቤት በመሄድ ዝርዝር የሕዝብና የቤት ቆጠራ መረጃዎችን ይሰበስባሉ::

75. የሕዝብና ቤት ቆጠራው አገሪቱን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ሲሆን በቆጠራውም የሚጠቃለሉት በቆጠራው ጊዜ የነበሩት ነዋሪዎች ናቸው:: በቆጠራው ማንም ሰው ሳይዘለል ማለትም ሳይቆጠር እንዳይቀር ወይም በድጋሚ እንዳይቆጠር ጥንቃቄ መደረግ አለበት:: በቆጠራው እያንዳንዱ ግለሰብ ተለይቶ ከተመዘገበ በኋላ ስለ ግለሰቡ የሚገልጹ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ብሔረሰብ፣ ሀይማኖት...ወዘተ መረጃዎች ይመዘገባሉ:: ከዚህም በላይ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚቆጠረው በአንድ በተወሰነ ቀን ማለትም የቆጠራውን ቀን ግንቦት 20/1999 መሠረት በማድረግ ሲሆን በዚህም መሠረት የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሚያመለክቱት በዚያ ቀን የነበረውን ሁኔታ ነው::

## ሐ. ቆጠራው የሚካሔደው መቼ ነው?

76. የ1999 ዓ.ም. ሦስተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች የሚከናወነው ከግንቦት 20-30 ቀን 1999 ዓ.ም ነው:: በመላ ሀገሪቱ የሚካሔደው ይህ ቆጠራ ሁሉንም ሰውና ቤተሰብ የሚመለከት ነው::

## መ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ መርሆዎች

77. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ እንደ ማንኛውም ሳይንሳዊ ጥናት ሁሉ በትክክል መሠራት አለበት:: ስለዚህ የሚከተሉት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሁለት መርሆች በማንኛውም ጊዜ ቢሆን መዘንጋት የለባቸውም::

## ማንኛውም የቤተሰብ አባል መቆጠር አለበት

78. ማንኛውም የቤተሰብ አባል መቆጠር አለበት ማለት በማንኛውም ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ አንድ የቤተሰብ አባል በዕድሜ ያረጀ ወይም ጨቅላ ሕጻን ቢሆንም የግድ መቆጠር አለበት ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሚጠቡ ሕጻናት ወይም በጣም ያረጁ ሰዎች ወይም የአእምሮ መታወክ ችግር ያለባቸው ሰዎች...ወዘተ በመረጃ ሰጭዎች አስተሳሰብ የማይፈለጉና የማይቆጠሩ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህ ግን በጣም ስህተት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የሕዝብ ቆጠራው ተግባር በሚከናወንበት ወቅት በእኩል ዓይን ታይቶ መቆጠር አለበት፡፡ ይህ የሁሉም ዜጎች እኩል መብት ነው፡፡ በዚህ ቆጠራ ህፃናትም ሆኑ የዕድሜ ባለፀጎች ሁሉም መቆጠር እንደሚገባቸው ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ በተለይም ህፃናት በቆጠራው ካልተካተቱ ብዛታቸው በትክክል ስለማይታወቅ መንግሥት ትምህርት ቤት ለመሥራት፣ መምህራንን ለማሰልጠን፣...ወዘተ ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ወቅት ችግር ሊገጥመው ይችላል፡፡ ከዚህም በላይ መገንዘብ የሚገባን የዛሬ ሕጻናት የነገ አዋቂዎች እንደሚሆኑና የሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባር በሚካሄድበት ጊዜ አንድ ሕጻን የአንድ ደቂቃ፣ የአንድ ሰዓት፣ የአንድ ቀን ወይም የአንድ ወር ዕድሜ እንኳ ቢኖረው መቆጠር ይገባዋል፡፡ በእድሜ ያረጁ ሰዎች፣ የአእምሮ መታወክ ችግር ያለባቸው ሰዎች ወይም በተለያየ ምክንያት በማህበረሰቡ የተገለሉ ሰዎች ሥራ መሥራት እንኳን ባይችሉ ሰው እንደመሆናቸው መጠን ፍጆታና አገልግሎት ስለሚያስፈልጋቸው በብሔራዊ/በአገር/ እቅድ ውስጥ መካተት ይገባቸዋል፡፡ ስለዚህም ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ሰው በዚህ ቆጠራ ሳይዘለል/ ሳይደገም መቆጠር ይኖርበታል፡፡

79. እንደሚታወቀው በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የሚኖር አንድ ሰው ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ቤተሰብን ይመሠርታሉ፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ ደግሞ ሕብረተሰብን ብሎም ከተማና የአስተዳደር ክፍሎችን ይመሰርታል፡፡ የእነዚህ አስተዳደር ክፍሎች ነዋሪዎች ተጠቃለው የኢትዮጵያን ሕዝብ ይመሠርታሉ፡፡ ስለዚህ ትክክለኛ የሆነ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ለማከናወንና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት አንድም ግለሰብ ከቆጠራው መገለል የሌለበት መሆኑን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ መቆጠር መብትም ግዴታም ነው የሚባለው ለዚህ ነው፡፡

## አንድ ሰው ሊቆጠር የሚገባው አንድ ጊዜ ብቻ ነው

80. አንድ ሰው ሊቆጠር የሚገባው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ማለት አንድ ግለሰብ በአንድ የቆጠራ ወቅት መቆጠር ያለበት አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ ይህ ነጥብ ሁሉም ልብ ሊለው የሚገባ ዓብይ መርህ ነው፡፡ በዚህ መርህ መሠረት አንድ ግለሰብ ከአንድ ጊዜ በላይ ማለትም ሁለት ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜ ሊቆጠር አይገባውም፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ከአንድ ጊዜ በላይ ተቆጠረ ማለት የሌለ የሕዝብ ቁጥር መረጃ ተሰበሰበ ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ

በተለይ የሌሉ ሰዎችንም በስህተት ስለሚጨምር መንግሥት በህዝቦች ጥቅም ላይ ተመስርቶ ሊሰራ ያሰበው የልማት ዕቅድ ለመዘርጋት ሲታሰብ የሀገሪቱ ጥሪትና ሀብት ለብክነት ይዳርጋል። ለምሳሌ በአንድ አካባቢ ላይ ለሚገኙ ሕፃናት አንድ የክትባት አይነት ለመስጠት ቢታሰብና በቆጠራው ወቅት ካሉት ህፃናት ውስጥ አንዳንዶቹ ተደግመው ቢቆጠሩ ከቆጠራው በኋላ ወደዚያ ቦታ የሚላከው የክትባት መድኃኒት መጠን አለአግባብ ይጨምርና ወደ ሌሎች አካባቢዎች የሚላከው መጠን አንሶ በመድሀኒት እጥረት ምክንያት ሕፃናት ሳይከተቡ ይቀራሉ። በአንፃሩ ሕፃናት በድጋሚ በተቆጠሩበት አካባቢ የመድኃኒት ብክነት ይከሰታል ማለት ነው። ስለሆነም የአንድ ሰው ከአንድ በላይ መቆጠር በቆጠራው መረጃ ላይ ከፍተኛ መፋለስን የሚያስከትል በመሆኑ በድጋሚ ተቆጥረው የተገኙ እንዲሁም በድጋሚ ለመቆጠር ጥረት ያደረጉ ሰዎች በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይደረጋል።

81. መንግሥት ለሕዝቡ አስፈላጊና በቂ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሀገሪቷና በየአስተዳደር ክልሉ የሚገኘውን የሕዝብ ብዛትና ባሕሪያት ማወቅ አለበት። ይኸውም የነዋሪውን ሕዝብ ብዛት በጾታ፣ በዕድሜ፣ ...ወዘተ ማለትም ምን ያህል ሕጻናት፣ልጆች፣ አዋቂዎች እንዳሉ መረጃ ማግኘት አለበት። ይህ መረጃ ለትምህርት ተቋማት ምን ያህል የተማሩ፣ ያልተማሩ፣ ብዛትና እንዲሁም አስፈላጊ ተቋማትን ለመመሥረት ግብዓት ሆኖ ያገለግላል። የሕዝቡን የሥራ ሥምሪት ሁኔታን በተመለከተ ከሥራ ከደረሰው ሕዝብ ምን ያህሉ በሥራ ላይ እንደ ተሰማራና ስንቱስ ሥራ አጥ እንደሆነ ...ወዘተ በትክክል ለማወቅ ይረዳል። ይህንንም በምሳሌ ማስረዳት ይቻላል። ለምሣሌ አንድ ልብስ ሰፊ ሸሚዝ ሱሪ ቀሚስ ለመስፋት ብትትን ጨርቅ ከመቆራረጡ በፊት የሚሰፋላቸውን ሰዎች ልክ መውሰድ ወይም መቀየስ እንደሚገባው ግልጽ ነው። ልብሱ የሚሰፋላቸው ሰዎች ልክ ካልወሰደ የሚሰፋው ሸሚዝም ሆነ ሱሪ ወይም ቀሚስ ለሰዎቹ ልክ አይሆንም። ማለትም ሊሰፋ፣ሊጠብ ወይም ሊረዝም ይችላል። ይህም ምሳሌያዊ አባባል የሚያስረዳው ከላይ የተጠቀሱትንና ከህዝብ ቆጠራ የሚገኙ መረጃዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ለማግኘት የሕዝብ ቆጠራ ሥራ በትክክል መከናወን እንዳለበት አመልካች ነው።

## ሠ. ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኙት መረጃዎች በሚስጥር የሚጠበቁ ስለመሆናቸው

82. በቆጣሪዎች አማካይነት ከእያንዳንዱ ግለሰብ የሚሰበሰበው መረጃ በሚስጥር የተጠበቀ ይሆናል። ይህም ማለት በቆጣሪዎችም ሆነ በሌሎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሠራተኞች የተሰበሰቡት መረጃዎች በሚስጥር መያዝ የሚገባቸው ስለሆኑ መንግሥት በጥብቅ ይቆጣጠራል ማለት ነው። በዚህም መሠረት በቆጣሪዎችም ሆነ በማንኛውም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሠራተኛ የተሰበሰቡት መረጃዎች በቃልም ሆነ በጽሁፍ እንዳይገለጹ በሕግ ተደንግጓል።

83. የቆጠራው ዓዋጅ ዋና አላማ እያንዳንዱ ግለሰብ ለሚቀርቡለት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ጥያቄዎች መረጃ በሚሰጥበት ወቅት ስለ ራሱና ስለ ቤተሰቦቹ የሚሰጣቸው መረጃዎች በሙሉ በተናጠል ለሌላ ለማንም አካል እንደማይገለጽ ለማሳወቅ ነው። ስለሆነም ማንኛውም መረጃ ሰጪ ምንም ዓይነት ፍርሃት ወይም ጥርጣሬ ሣይገባው መረጃ መስጠት ይኖርበታል። የቆጠራው ዓላማ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚሰጠውን መረጃ ነጥሎ በማውጣት ማሳየት ሳይሆን ይልቁንም የብዙ ግለሰቦችን መረጃዎች ማለትም የሀገሪቱን ሕዝብ በአጠቃላይ የሚመለከቱ መረጃዎችን ማቅረብ ነው። ለምሳሌ ያህል መረጃው በአንድ ከተማ ውስጥ ምን ያህል ሰዎች እንዳሉ፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በትምህርት ደረጃ ... ወዘተ ለማመልከት እንጂ በከተማው ነዋሪ የሆኑት አቶ አገሌ ወይም ወ/ሮ አገሌትስንት ልጆች እንዳሉዋቸው ስማቸውን ወይም እድሜአቸውን፣ ... ወዘተ የሚመለከት ግለሰባዊ መረጃ ለማሰራጨት አይደለም። የሕዝብና ቤት ቆጠራው ውጤት የግለሰብን መረጃ ነጥሎ በማውጣት ሪፖርት ለማቅረብ ሳይሆን አጠቃላይ የሀገሪቱን ሕዝቦች ማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚያመለክት መረጃ አጠናቅሮ ለማሰራጨት መሆኑን ሁሉም ዜጋ በጥንቃቄ ሊያጤነው ይገባል።

## ረ. ከሕብረተሰቡ የሚጠበቅ ትብብር

84. የቆጠራውን ሥራ በተሳካና በተቀነባበረ ሁኔታ ከዳር ለማድረስ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ/በኢትዮጵያ የሚኖር ማንኛውም ሰው ድጋፍና ትብብር ወሳኝ ነው። ይህ ደግሞ የእያንዳንዳችንን ጥረት የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም የህዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በጣም ግዙፍና ውስብስብ በመሆኑ በሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት (በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ) ብቻ ሊከናወን የማይችል ሥራ ስለሆነ ሁሉም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ቤተሰቦችና እንዲሁም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በዚህ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ከፍተኛ ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

85. በዚህም መሠረት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ/በኢትዮጵያ የሚኖር ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ተግባራት በኃላፊነት ስሜት መፈፀም ይጠበቅበታል።

- ቆጣሪዎች ለቆጠራው ሥራ ወደየቤታችን በሚመጡበት ጊዜ እቤት በመገኘት አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ። በተለይ ለሚጠይቁን ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን፣
- ለሚጠየቁት ጥያቄዎች የምንሰጠው ምላሽ ለአገር ግንባታ፣ ለልማት ዕቅዶችና ለሕዝብ ጠቀሜታ የሚውል መሆኑን ተረድተን ትክክለኛ መልስ መስጠት፣

- በሚገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለቆጠራው ዓላማ ጠቀሜታ ለጎረቤቶቻችን፣ ለጓደኞቻችን እንዲሁም ለዘመዶቻችን ማስረዳት፣ በተለይ ላልተማሩ ወገኖች ቆጠራውን የሚመለከቱ መፈክሮች (ተለጣፊ/ተንጠልጣይ) ወይም የሚበተኑት ወረቀቶች ምን እንደሚሉ ማብራራት . . . ወዘተ ይሆናል፡፡

## ሰ. በየደረጃው ከሚገኙ የመስተዳድር አካላት የሚጠበቅ ትብብር

86. የሕዝብና ቤት ቆጠራውን ሥራ ተግባራዊ ለማድረግ ከሁሉም የመስተዳድር አካላት አያሌ ትብብሮች ይጠበቃሉ፡፡ ከነዚህም ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ወቅት፣

⇒ ለካርታ ሠራተኞች መጠለያ በማዘጋጀት ትብብር ማደረግ/፣

⇒ የየወረዳውን ወይም የቀበሌውን ትክክለኛ ድንበር የሚያውቅሰው በመመደብ መተባበር፣

⇒ የካርታ ሠራተኞች ለሚጠቀሙባቸው ልዩ ልዩ ንብረቶች ተገቢው ጥበቃ የሚደረግበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

⇒ የድንበር አለመግባባት በሚከሰትበት ጊዜ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን አፋጣኝ መፍትሔ እንዲገኝ ማድረግ፡፡

### በቆጠራው ወቅት

⇒ ለቆጠራ ሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች (ቆጣሪዎች፣ ተቆጣጣሪዎች...ወዘተ) መጠለያ እና የምግብ አቅርቦት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

⇒ ቆጠራው በሚከናወንበት ወቅት ቤቶችና ቤተሰቦች ያሉበትን ቦታ በትክክል ለቆጣሪው ሊያሳይ የሚችል መንገድ መሪ መመደብ፣

⇒ የቆጠራ ሠራተኞች ለሚገለገሉባቸው ልዩ ልዩ ንብረቶችና የቆጠራ መጠይቆች ተገቢውን ጥበቃ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

⇒ በቆጠራው ወቅት ህብረተሰቡ የቆጠራውን ዓላማና ጥቅም አውቆ ተገቢውን ትብብር እንዲያደርግ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ናቸው

## ሸ. ግዴታና ቅጣት

87. ማንኛውም ግለሰብ በሕዝብ ቆጠራው ቆጣሪ ወይም ተቆጣጣሪ ጥያቄ ሲቀርብለት ስለራሱ ትክክለኛ የሆነ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ይህንን ግዳጅ ለመፈፀም ፈቃደኛ ባይሆን የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር

449/1997 አንቀጽ 14 መሠረት እስከ 6 ወራት በሚደርስ እስራት ይቀጣል። ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ሲሆን ከብር 2 ሺህ /ሁለት ሺህ ብር/ በማይበልጥ ገንዘብ ይቀጣል።

88. በቆጠራው ወቅት ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም መረጃ ወደሚሰበሰብበት ቤት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ንብረት ገብቶ የቆጠራ መረጃ የማግኘት ሥራን ያሰናከለ እንደሆነ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል። ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ደርጅት ሲሆን ከብር 5 ሺህ /አምስት ሺህ ብር/ በማይበልጥ ገንዘብ ይቀጣል።

## XIII . የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትምህርትና ቅስቀሳ ዓላማዎች

### ሀ. ዓላማ፡

89. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በጣም ግዙፍ፣ በርካታ የገንዘብ ወጭና ብዙ የሰው ኃይል የሚያስፈልገው በመሆኑ የአንድ መ/ቤት ወይም ድርጅት ኃላፊነት ብቻ ሊሆን አይችልም። ከቆጠራው የሚገኙት ውጤቶች በመንግሥትና በሌሎች የቆጠራ ውጤት ተጠቃሚዎች ዘንዱ ተፈላጊነታቸው ከፍ እያለ መጥቷል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ በቆጠራው የሚሰበሰቡ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ መረጃዎች ለልማት ሥራዎች የሚኖራቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘቡ ለቆጠራው ያለው ግንዛቤ እያደገ መጥቷል። ይህም ሆኖ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ግብ መምታት በአብዛኛው የሚወሰነው የቆጠራው ሥራ ጠቃሚነት በህብረተሰቡ ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት ሲኖረውና ህብረተሰቡ ለሥራው በከፍተኛ ደረጃ ሲተባበር ብቻ ነው። በመሆኑም በሕዝቡ ዘንድ የቆጠራው ጠቀሜታ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ ቆጠራውን አስመልክቶ ጥልቀትና ስፋት ያለው የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ማካሄዱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

90. የቆጠራው የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ህብረተሰቡን ስለቆጠራው ጥቅም ማሳመን መቻል ያለበት ሲሆን ይህም ሊፈፀም የሚችለው ህብረተሰቡን በሕዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቆች ውስጥ የተካተቱትን ጥያቄዎች እንዴት መመለስ እንዳለባቸው የሚሰበሰቡት መረጃዎች በምን ጥቅም ላይ እንደሚውሉ በማስተማርና በማሳወቅ ሊኖር የሚችለውን ጥርጣሬ የማስወገድ አቅም ሲኖረው ነው። የቆጠራው ሥራ የተሳካ እንዲሆንና ብሎም የተሟላ፣ ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃዎች ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ለማግኘት እንዲቻል የቆጠራው የመስክ ሥራ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ ቆጠራው በመካሄድ ላይ እያለ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ማካሄድ ያስፈልጋል። የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ቀዳሚ ዓላማ ለቆጠራው አፈጻጸም መሳካት የሕዝቡን ሙሉ ትብብር፣ ከፍተኛ ድጋፍና ተሳትፎ ለማግኘት፣ ስለቆጠራው ምንነት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ለማሳወቅ ነው። ዋና ዋና ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

- በግንቦት ወር 1999 ሊካሄድ ስለታቀደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ምንነት በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁም በሕዝቡ ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ፣
- ስለ ቆጠራው ጠቃሚነትና አስፈላጊነት ለሕዝቡ ማሳወቅ፣
- ከቆጠራው የሚገኙ መረጃዎችን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በመረዳት ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት የሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት ያልተቆጠበ ድጋፍና ትብብር ለቆጣሪዎች ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ማሳወቅ እና
- ከቆጠራው የሚገኘው ውጤት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ማስቻል ነው።

## ለ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የሚካሄድባቸው ዘዴዎች

91. የቆጠራው የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ሊካሄድ ከሚችልባቸው ዘዴዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች፣ የሕትመት ላይ መልዕክቶች እና የመድረክ ላይ ቅስቀሳ ናቸው። እነዚህ ዘዴዎች ስለቆጠራው ለማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልዕክቶች ለሕብረተሰቡ በማድረስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

### በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች የሚከናወን የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ

92. ሀ. በሬዲዮና በቴሌቪዥን ጣቢያዎች አማካይነት /በሁሉም ቋንቋዎች/ ስለቆጠራው ቃለመጠይቆችን፣ የፖናል ውይይቶችን፣ ማብራሪያዎችንና ድራማዎችን እያዘጋጁ ማስተላለፍ።

ለ. በየዝግጅቶቹ ጣልቃ የሚሰራጩ መፈክሮችንና አጫጭር መልዕክቶችን በመዝሙር አጅቦ በማስቀረጽ እንዲተላለፍ ማድረግ፣

ሐ. በመንግሥት በሚታተሙ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ስለቆጠራው የሚያሳውቁ መፈክሮችን፣ አጫጭር ጽሁፎችንና ካርቱኖችን አዘጋጅቶ እንዲታተሙ ማድረግ፣

### የመድረክ ላይ ቅስቀሳ ሥራ

93. የመድረክ ላይ ቅስቀሳ ሥራ በሴሚናሮች፣ በስብሰባዎችና ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ማለትም አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማት፣ መስጊዶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፊልምና ትያትር ቤቶች ወዘተ ስለሕዝብና ቤት ቆጠራ አጠቃላይ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች መስጠትን ያጠቃልላል።

## የህትመት ላይ ጽሑፎች

94. በሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች በሚታይ መልኩ መፈክሮችንና ፖስተሮችን መለጠፍ/ማንጠልጠልና በሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች የሚሰራጩ በራሪ ድሁፎችን በመበተንና የመሳሰሉትን ቅስቀሳዎች ያጠቃልላል፡፡

## ሐ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ አፈጻጸም ሁኔታ

95. የትምህርትና ቅስቀሳው ሥራ በተያያሉ ደረጃዎች እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

- በተለያዩ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች መግለጫዎች መስጠት፣
- ከአገር አቀፍ ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ የቆጠራውን ሥራ የማስተባበርና የመምራት ኃላፊነት ለሚሰጣቸው ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎችና ሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች ሴሚናር ማካሄድ፣
- ቆጠራውን በሚመለከት በየደረጃው በሚሰጠው ሴሚናር ላይ በሚሳተፉ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት ለህብረተሰቡ ስለ ቆጠራው ምንነት፣ አሠራር፣ ጥቅምና አስፈላጊነት ማስተላለፍ፡፡

96. በአጠቃላይ የቆጠራው ቅስቀሳ ሲካሄድ በተከታታይ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ይኸውም ቆጠራው ከመጀመሩ ትንሽ ቀደም ብሎ ስለ ቆጠራው ዓላማና ጥቅም በቆጠራው ስለሚሰበሰቡ መረጃዎች፣ መረጃዎቹ በሚስጥር የሚጠበቁ ስለመሆኑ ማሳወቅ፤ በተከታታይም በቆጠራው ስለሚሰበሰቡ መረጃዎች ዝርዝር፣ ስለ መጠይቁ አሞላል እንዲሁም እያንዳንዱ ግለሰብ ሳይቆጠር እንዳይቀር ወይም በድጋሚ እንዳይቆጠር ማብራራትና ማሳወቅ ናቸው፡፡

## መ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ላይ የሚሳተፉ አካላት

97. የቆጠራውን የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ለማከናወን የተያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን፣
2. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣
3. የማስታወቂያ ሚኒስቴር ፣
4. የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት፣ የክልል ቴሌቪዥን ፕሮግራሞችና ሬድዮ ጣቢያዎች፣
5. የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣

6. የኢትዮጵያ ኘሬስ ድርጅት፣
7. ቆጠራውን በየደረጃው የሚመሩና የሚያስተባብሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣
8. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሥነ ሕዝብ ጉዳይ መምሪያ፣
9. UNFPA (የተባበሩት መንግሥታት የህዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት)
10. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን መዋቅር ውስጥ በትምህርትና ቅስቀሳ ዘርፍ የተመደቡ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣
11. ሕዝባዊ ድርጅቶች /የወጣቶችና የሴቶች ... ወዘተ/፣
12. የገጠርና የከተማ ቀበሌ መስተዳድሮች፣
13. ትምህርት ቤቶች /መምህራንና ተማሪዎች/፣
14. የኃይማኖት ድርጅቶች፣
15 የቆጠራውን የመስክ ሥራ የሚያከናውኑ ሠራተኞች /ተቆጣጣሪዎችና ቆጣሪዎች/።
16. የግል ሬድዮ፣ ፕሬስ አገልግሎቶችና የዜና ወኪሎች
17. የማህበረሰብ ድርጅቶች /ዕድር ...ወዘተ/
18. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

## ሠ. በትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የልዩ ልዩ አካላት ተሳትፎ

8. ከላይ የተዘረዘሩት አካላት በህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ትምህርትና ቅስቀሳ ስራ ላይ ሊኖራቸው የሚችለው ተሳትፎ እንደሚከተለው ተገልጿል።

### *የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን*

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራዎችን የትምህርትና ቅስቀሳውን ጨምሮ በበላይነት የመምራት የመቆጣጠርና የማስፈፀም ተግባራትን ያከናውናል።

### *የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ*

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት እንደመሆኑ ሁሉ ማናቸውንም የቅስቀሳ ዶክመንቶችንና መመሪያዎችን የማዘጋጀትና የዕለት ተዕለት ሥራውን በመከታተል የማስፈፀም ተግባራትን ያከናውናል።

### *ማስታወቂያ ሚኒስቴር*

ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደየመንግሥት ቃል አቀባይ መ/ቤትነቱ የሕዝብና ቤት ቆጠራው በውጤታማነት ይጠናቀቅ ዘንድ በመንግሥት በኩል መደረግ ያለበትን፣ እና እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በመከታተል ለሕብረተሰቡ የማሳወቅ ተግባራትን ያከናውናል።

## *የኢትዮጵያ ሬድዮ፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና የክልል ሬድዮ ጣቢያዎች*

ቆጠራውን በተመለከተ ለሚዘጋጁ ውይይቶች፣ ጥያቄና መልሶች፣ ማብራሪያዎች፣ መፈክሮች፣ ድራማዎች፣ መዝሙር እና መሰል ዝግጅቶች በቂ የአየር ሰዓት በመስጠትና በየዝግጅቶቻቸው ጣልቃ በማስገባት በየሥራ ቋንቋዎቻቸው የማሰራጨት ተግባራትን ያከናውናሉ።

## *የኢትዮጵያ ኘሬስ ድርጅት*

በመንግሥት ቁጥጥር በልዩ ልዩ ቋንቋዎች በሚታተሙ ልዩ ልዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ቆጠራውን በተመለከተ ለሚዘጋጁ መፈክሮች፣ አጫጭር መግለጫዎች፣ ካርቱኖችና መሰል ዝግጅቶች ከቆጠራው ቀን በፊት ጀምሮ ቦታ በመስጠት እየታተሙ እንዲወጡ ይደረጋል።

## *ቆጠራውን በየደረጃው /በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌ/ የሚመሩና የሚያስተባብሩ የመንግሥት መ/ቤት ኃላፊዎችና የሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች*

የቆጠራው ሥራ ለማስፈፀም የሚወጡ መመሪያዎች፣ ለማስፈፀም በሚንቀሳቀሱባቸው ጊዜያት፣ በሚያካሂዷቸው ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች ወዘተ ሁሉ የቆጠራውን ይዘትና ምንነት ለሚመለከታቸውና ለሚያገኟቸው አካላት በማሳወቅ ረገድ ጉልህ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎችን እንዲያካሂዱ ይጠበቃል።

## *የሥነ ሕዝብ ጽ/ቤት*

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የሚመለከተው በመሆኑ ቆጠራው በተሳካ ሁኔታ እንዲከናወን የሚረዳ የቅስቀሳ መድረኮችን ያዘጋጃል፣ አፈፃፀማቸውንም በተመለከተ ያስተባብራል።

## *UNFPA (የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት)*

ለቆጠራው ሥራ የሚውሉ የቅስቀሳ ዶክመንቶችንና ቁሳቁሶችን ማደራጃ የሚሆን የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ያደርጋል።

## መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

የቆጠራው ተግባር የሚመለከታቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች /እንደ አካል ጉዳተኞች ፌዴሬሽን/ ያሉ ለትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የሚውሉ ቁሳቁሶችን የማዘጋጀት እና የቅስቀሳ መድረኮችን የማመቻቸት ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

## በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን መዋቅር ውስጥ በትምህርትና ቅስቀሳ ዘርፍ የተመደቡ ሠራተኞች

ለትምህርትና ቅስቀሳ ተግባራት ይውሉ ዘንድ በማዕከል የተዘጋጁ መመሪዎችን፣ ቡሮሹሮችን፣ አጫጭር መግለጫዎችን፣ ፖስተሮችን መፈክሮችን፣ መዝሙሩን እና መሰል የትምህርትና የቅስቀሳ መሳሪዎችን ከማዕከል ወደየአካባቢዎቻቸው በማድረስ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፡፡ ቆጠራው ከመካሄዱ በፊት እና በሚካሄድበትም ወቅት ሕብረተሰቡ ስለቆጠራው ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያግዙ ቡሮሹሮችን የማሰራጨት፣ ፖስተሮችን የማስለጠፍ፣ በተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪዎች በመዘዋወር መዝሙር፣ መፈክሮችንና መልዕክቶችን በማሰማት የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳሉ፡፡ በአጠቃላይ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራን በባለቤትነት ያካሂዳሉ፡፡

## ሕዝባዊ ድርጅቶች /የቀበሌና የገበሬ ማህበራት/

ሕብረተሰቡን በቅርብ ለማግኘት የሚያስችሉት እነዚህ ማህበራት ስለሆኑ የየአካባቢውን ሕብረተሰብ ሰብስቦ ለማነጋገር፣ ስለቆጠራው አስፈላጊውን ትምህርትና ቅስቀሳ ለማካሄድ፣ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ለማሟላት ወዘተ. በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ከፍተኛ መድረኮችን የማመቻቸት ሥራዎችን ይሰራሉ፡፡

## በትምህርት ቤቶች /መምህራን እና ተማሪዎች/

በትምህርት ቤቶች አካባቢ በቀላሉ ተሰብስበው ስለሚገኙ የቆጠራውን ዓላማና የመጠይቆችን ይዘት በመጀመሪያ ለመምህራንና ለተማሪዎች በማሳወቅ የተዘጋጁ ቡሮሹሮችንና መሰል የትምህርትና የቅስቀሳ መሳሪያዎችን እንዲደርሷቸው በማድረግ ለየቤተሰቦቻቸው እንዲያሳውቁ እንዲያብራሩ...ወዘተ. በማድረግ ጉልህ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራን ያከናውናሉ፡፡

### የኃይማኖት መሪዎች

የሁሉንም ኃይማኖት መሪዎች ቀድሞ በማግኘትና የቆጠራውን ይዘትና ዓላማ በማሳወቅ ለየኃይማኖቶቹ ተከታዮች በየማምለኪያ ቦታዎቻቸው እንዲያሳውቁ፣ በቆጠራው ጊዜም የሚጠየቁትን ጥያቄ በአግባቡ እንዲመልሱ የአደራ መልዕክት እንዲያስተላልፉ በማድረግ ጉልህና ትርጉም ያለው የቅስቀሳ ሥራ ይሰራሉ።

### የቆጠራውን የመስክ ሥራ የሚያከናውኑ ሠራተኞች /ቆጣሪዎች እና ተቆጣጣሪዎች/

ትክክለኛውን መረጃ የማግኘትና የማምጣት የሥራ ኃላፊነቱ ይበልጥ የሚወድቀው፣ በቆጣሪዎች እና በተቆጣጣሪዎች ላይ እንደመሆኑ ሁሉ ይህንኑ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ እንዲቻላቸው በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ለሚገኙ ቤተሰቦችና ግለሰቦች ሁሉ የቆጠራውን ዓላማና ለወደፊት የሚሰጠውን ጥቅም ለህብረተሰቡ የማሳወቅ ተግባራትን ይፈጽማሉ። በየቀበሌው በገጠርና በከተማ የቆጠራው ቀን እንዲከበር በማስተባበር ይሳተፋሉ።

## XIV. ከቆጠራው በኋላ ስለሚከናወኑ ተግባራት

### ሀ. መረጃውን በኮምፒውተር ማቀነባበር

99. ለቆጠራ ሥራ የዋሉ ዶክመንቶች ማለትም የተሞሉመጠይቆችና ሌሎች ቅጾች፣ እንዲሁም ካርታዎች የቆጠራ ሥራው እንደተጠናቀቀ ወደ ማዕከላዊው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት መመለስ ይኖርባቸዋል። ከዚያም በሕዝብና ቤት ቆጠራው መጠይቅ የተሞሉትን መረጃዎች በማረምና ኮድ በማድረግ ወደ ኮምፒዩተር እንዲገቡና እንዲቀነባበሩ ይደረጋል።

100. መጠይቆች በአግባቡና በትክክል መመለሳቸውን ለማረጋገጥና በኃላም በዋናው መ/ቤት ቅንብር ወቅት በስርዓት እንዲቀመጡና ስራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ እንዲቻል መጠይቆች በቆጠራ ቦታ፣ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በከተማ፣ በዞን፣ በክልል ተለይተው የሚቀመጡበት ቦታና ሁኔታ ይደራጃል፣ አንዱ ከአንዱ የሚደባለቅበት ሁኔታ እንዳይኖር መጠይቆች በቦርሳ ውስጥ ይያዛሉ።

101. የህዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቆች ሲሞሉ እያንዳንዱ ቆጣሪ ለሚሠራበት ቆጠራ ቦታ ስለህዝቡ ብዛት ማጠቃለያ ስለሚያዘጋጅ እነኚህ ማጠቃለያዎች ከቆጠራው መጠይቅ ጋር በዋናው መ/ቤት መጥተው ፈጠን ባለ ሁኔታ በአንድ ላይ ይጠናቀራሉ። ጥልቀት ያለው የትንተና ሥራ ተጠናቆ

ውጤት እስከሚገኝ ድረስ ቆጠራው በተካሄደ በሶስት ወር ጊዜ የመጀመሪያ ደረጃ አጠቃላይ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ይቀርባል::

### ለ. የድህረ ቆጠራ ጥናት ማካሄድ

102. ድህረ ቆጠራ ጥናት በዋናው የህዝብና ቤት ቆጠራ የተሰበሰበውን መረጃ ትክክለኛነት ለመገምገም እንዲቻል በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች ባሉ ቤተሰቦች ላይ የድህረ ቆጠራ ጥናት ይካሄዳል::

### ሐ. ከቆጠራው የተገኘው መረጃ መገምገም፣ መተንተንና ሪፖርት ማዘጋጀት፣

103. ከቆጠራው የተገኘው መረጃ በኮምፒዩተር ከተቀነባበረ በኋላ ውጤቱ በሰንጠረዥ ይወጣል:: ይህ መረጃ ትክክለኛነቱ በሚገባ ከተገመገመ በኋላ ግኝቱ ምን እንደሚመስል ይተነተናል:: ከዚያም የትንተናው ውጤት በሪፖርት መልክ ተዘጋጅቶ ይወጣል:: እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ባላቸው አገሮች የተሰበሰበውን መረጃ አርሞና በኮምፒዩተር አቀነባብሮ በአገር አቀፍና በአስተዳደር አካባቢ ተንትኖ ሪፖርት ለማዘጋጀት በኮምዩተር ዕውቀት የተደራጀ ሙያተኛ የሰው ኃይል ስለሚያስፈልግ የሚወስደውን ጊዜ እየተሻሻለ ከመጣውና ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ላይ ከሚውለው የስካኒንግ ቴክኖሎጂ ጋር ሲገናዘብ ባለፉት ሁለት ቆጠራዎች ከተወሰደው ጊዜ እጅግ በጣም እንደሚያንስ ይገመታል::

### መ. የቆጠራውን ውጤት የሚያሳዩ ሪፖርቶችን ለመረጃ ተጠቃሚዎች ማሰራጨት

104. ከሕዝብና ቤት ቆጠራ ተግባራት መሃከል የመጨረሻው የቆጠራውን ውጤት የሚያሳዩ ሪፖርቶች በመረጃው ተጠቃሚ ለሆኑ መንግሥታዊ፣ ሕዝባዊና የግል ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች እንዲሁም በምርምር ሥራ ለተሰማሩ ሁሉ ማሰራጨት ይሆናል:: የሥርጭቱም መንገድ የታተሙ መጽሔቶችን በነፃና በግዢ ለማንኛውም ተጠቃሚ ማቅረብና ማሰራጨት፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በነፃና በግዢ ማቅረብ፣ በሴሚናሮች ለህዝብ ማስታዋወቅን... ወዘተ ይጨምራሉ::

### ሠ. ጥልቀት ያላቸው ጥናቶችን ማካሄድ

105. የቆጠራው አጠቃላይ ውጤት ለተጠቃሚዎች ከተሠራጨ በኋላ፣ ዝርዝርና ጥልቅ ጥናቶች በኮሚሽኑ ጽ/ቤት (በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ)፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በተመራማሪዎች እንደሚደረጉ ይጠበቃል::